# የኢትዮጵያ የ2011/2012 የሰብዓዊ መብቶች ሪፖርት

## አጭር ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ፌዴራል ሪፑብሊክ ናት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) በመባል የሚታወቀው በብሄር የተደራጁ ድርጅቶች ቅንጅት የብልጽግና ፓርቲ ታህሳስ 2012 ተክቶት እስከተመሰረተ ድረስ መንግሥትን ይቆጣጠር ነበር፡፡ በ2007 በተካሄደው አጠቃላይ ምርጫ ኢሕአዴግ እና አጋር ድርጅቶች፣ 547 የፓርላማ መቀመጫዎችን በሙሉ አሸንፈው ግንባሩ ለአምስተኛ ተከታታይ ጊዜ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ቻለ፡፡ የካቲት 2011፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ትዕግስቱ እየተሟጠጠ የመጣውን የወጣቱን ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲቻል የፖለቲካ ማሻሻያዎችን ለማፋጠን በሚል ምክንያት ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እንደሚለቁ አስታወቁ፡፡ ሰፊ የለውጥ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ አቢይ አሕመድ አሊን ሚያዝያ 2011 ፓርላማው ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሾማቸው፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ መንግስት ሕግን ማስከበር ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ሆኗል። የፌዴራል ፓሊስ ጥቅምት 2011 ለተመሰረተው የሰላም ሚኒስቴር ሪፓርት እንዲያቀርብ የተደረገ ሲሆን ፓርላማው የበላይ ቁጥጥር ያደርግበታል፤ ሆኖም ግን ፓርላማው የበላይ ቁጥጥር የማድረግ አቅሙ ውስን ነው፡፡ እያንዳንዳቸው ዘጠኙ ክልላት የራሳቸው የሆኑ የክልል ልዩ ኃይል ወይም የፖሊስ ሠራዊት ወይም ሁለቱም አላቸው፤ እነዚህም ለክልሉ የሲቪል ባለሥልጣናት ሪፓርት ያደርጋሉ፡፡ የአካባቢ ሚሊሺያዎች በአገሪቷ ዙሪያ ላላ ባለ እና በተለያየ መልክ ከክልል ፓሊስ፤ ከፌዴራል ፓሊስ እና ከጦር ሃይል ጋር በመተባበር ጥበቃ ላይ ተሰማርተው ይሰራሉ፡፡ በማህበረሰብ መሪዎች የተመረጡ የአካባቢ ሚሊሺያዎች በአካባቢያቸው መደበኛ የጸጥታ ሥራ ለማካሄድ ሥልጣን ይሰጣቸዋል፤ በዋነኛነት በገጠራት፡፡ በብዛት የሚቀርቡት ዘገባዎች እንደሚያሳዩት የክልል የሲቪል ባለሥልጣናት በክልል የጦበቃ ሃይሎች ላይ አንዳንድ ጊዜ ቁጥጥር ማድረግ ያቅታቸዋል፡፡ ገጠር ያሉ የአካባቢ ፓሊሶች እና ሚሊሺያዎች በራሳቸው ፈቃድ እና ከፍትህ ውጪ እርምጃ ይወስዳሉ። የአካባቢ መንግስት ባለሥልጣናት ለተመረጡ ሚሊሺያዎች በጣም መሰረታዊ የሆነ ሥልጠና ይሰጣሉ፤ የሚሊሺያ አባላት በማህበረሰቡ እና በአካባቢው ፓሊስ መሃከል ድልድይ በመሆን መረጃ በማቀበል እና ሕግን በማስከበር ያገለግላሉ፤ የማህበረሰቡ ጥበቃ አካላት ሕግን እና ሥርዓትን ማስጠበቅ ባልቻሉ ጊዜ የአገር ውስጥ ደህንነትን ለማስጠበቅ የጦር ኃይል የዕዝ ጣቢያ በማቋቋም በተለይ እንደ ምዕራብ እና ደቡብ ኦሮሚያ አካባቢ እንዲሁም በደቡብ ብሄር፤ ብሄሮች፤ እና ሕዝቦች ክልሎች ውስጥ ሰፊ ሚና ተጫውተዋል፡፡

አቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ አዎንታዊ ለውጦች መምጣት ጀመሩ፡፡ መንግሥታቸው ቀደም ሲል በአገር ክህደት የተከሰሱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ከወንጀል ፍረጃ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ መሪዎች ወደ አገሪቱ ተመልሰው እንዲንቀሳቀሱ እንዲሁም ሰላማዊ ሰልፎችን ማድረግ እንደሚቻል ተፈቅዶ ከተጽዕኖ ነጻ የሆኑ አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሚዲያ ተቋማት እንዲመሰረቱ ተደረገ፤ በተጨማሪ በሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞች ከእስር የሚፈቱባቸው እርምጃዎች ተወስደው አፋኝ ሕጎች እንዲከለሱ ተደረገ፡፡

ሰኔ 15 የተፈጸመውን የመንግሥት ባለሥልጣናት ግድያ ተከትሎ ለምርመራ በቂ ጊዜ ለማግኘት በሚል ሰበብ መንግሥት ከቅርብ ወራት ወዲህ ጸረ ሽበርተኝነት አዋጅን መጠቀም ጀምሯል። በተጨማሪም አገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ደህንነታቸው ሳይጠበቅ፤ ፈቃደኛ ሳይሆኑ እና ክብራቸውን በሚነካ ሁኔታ ወደ መጡበት እንዲመለሱ ተደረገዋል ሲሉ ሰብዓዊ ድርጅቶች ዘግበዋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህን የተፈናቀሉትን ሰዎች ለመንገብኘት መከልከላቸው በዋነኘነት የሚያሳስባቸው ጉዳይ እንደሆነ አሳውቀዋል፡፡

*ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች የሚያጠቃልሉት፡- በደህንነት አባላት በሕገወጥ እና በዘፈቃደ የሚካሄዱ ግድያዎች፤ ዜጎች ሌሎች ዜጎችን በብሔራቸው ላይ ተመስርተው መግደላቸው፤ ባልታወቀ ሁኔታ መሰወር፤ በደህንነት አባላት በሕገወጥ እና በዘፈቃደ መያዝ እና መታሰር፤ አስከፊ እና ለሕይወት አደገኛ የሆኑ የእስር ቤት ሁኔታዎች፤ ግላዊነት ላይ ሕገወጥ ጣልቃ ገብነት፤ ሳንሱር ማድረግ፤ ኢንተርኔት እና የማህበሪያዊ ሚዲያዎችን ማገድ፤ አንድ አይነት ጾታ ባላቸው መሀከል የሚከናወነውን የወሲብ ወንጀል ማድረግ እና አስከፊ የሆኑ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛዎች ዋንኛዎቹ ናቸው፡፡*

*መንግሥት በተለይ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ በነበሩ ሹሞች ላይ ሰብዓዊ መብት ጥሳችኋል በማለት የመክሰስ እርምጃ ወስዶባቸዋል፤ ቢሆንም ግን መንግሥት በይቅርታ የቀረጸው የእርቅ ጥረት ፓሊሲውን በመጠቀም አነስተኛ ደረጃ ላላቸው ባለሥልጣናት ይቅርታ አድርጓል፡፡ በደህንነት ሃይሎች እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል በአብይ ጊዜ መንግሥት ተጠያቂነቱን በሚመለከት አዎንታዊ እርምጃዎችን ወስዷል። በንሃሴ 2011 በቀድሞ የሱማሊያ ክልል ፕሬዝዳንት አብዲ መሃመድ አማር እና በሌሎች ላይ የወንጀል ሴራ ጠንስሳችኋል እንዲሁም ለአመጽ መሳሪያ አንስታችኋል በማለት የፌዴራል አቃቢ ሕግ የወንጀል ክስ አቅርቧል ፡፡ ጌታቸው አሰፋ፣ አሰፋ በላይ፣ ሺሳይ ልዑል እና አጽበሃ ግደይ ላይ አሰቃቂ እና ዒሰብዓዊ የሙብቶች ጥሰት እና ሙስና ፈጽመዋል ሲል የፌዴራል አቃቢ ሕግ የወንጀል ክስ አቅርቧል፤ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉም የቀድሞው የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ከፍተኛ ባለሥልጣናት የነበሩ ናቸው። ፓሊስ ተከሳሾቹን በትግራይ ክልል ማግኘት ባለመቻሉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሾቹ ባልተገኙበት ክሱ እንዲቀጥል ሐምሌ 9 ቀን አዟል፡፡*

## ክፍል ፣፡- የሰውን ልጅ በሰውነቱ ማክበር፣ ከዚህ ከሚከተሉት እና ከሌሎችም ነጻ መሆን

### *ሀ. በዘፈቀደ ሕይወትን ከማሳጣት፣ እንዲሁም ሌሎች ከሕገ ውጪ እና በፖለቲካ ምክንያት ከሚፈጸሙ ግድያዎች*

*መንግሥት እና ወኪሎቹ የዘፈቀደ እና ሕገወጥ ግድያዎችን ስለመፈጸማቸው በርካታ ሪፖርቶች ነበሩ፡፡ የጸጥታ ኃይሎች በሰላማዊ ዜጎች ላይ ለግድያ የሚያደርስ ኃይል ተጠቅመዋል፡፡*

*በምዕራብ ጎንደር አማራ ክልል ውስጥ በሲቪሎች የተዘጋውን መንገድ ለማስከፈት የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከሊያ ሃይል ታህሳስ 30 ባደረገው ሙከራ ተኩስ ተከፍቶ ዘጠኝ ሰዎች ሞተዋል። አደጋው በተፈጸመ ጊዜ የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት የነበሩት ገዱ አንዳርጋቸው በይፋ ግድያውን አውግዘዋል፣ መርማሪ ቡድንም ወደ ቦታው ልከዋል፡፡*

*ሰኔ 15 ባህር ዳር ውስጥ የታጠቀ ሃይል የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት አምባቸው መኮንንን እና የአማራ ክልል መንግሥት አማካሪ እዘዝ ዋሴን አጥቅቶ ገድሎአል። ሰኔ 15 በደረሰበት መቁሰል ምክንያት የአማራ ክልል አቃቢ ሕግ ምግባሩ ከበደ ሰኔ 17 ሕይወቱ አልፏል። ባህር ዳር ውስጥ የደረሰውን ጥቃት በመከተል በሰዓታት ውስጥ ጄኔራል ሰአረ መኮንን የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሃይሎች መሪን እና ጡረታ ላይ የነበሩትን የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሃይሎች የሎጅስቲክ ሃላፊ ጄኔራል ገዛይ አበራን አዲስ አበባ ውስጥ ጥበቃ ላይ የነበረ ዘብ ገደላቸው፡፡ ሰኔ 17 ባህር ዳር አካባቢ በተካሄደ ቁጥጥር ሥር የማዋል እርምጃ የጥበቃ ሃይሎች መኮንንን እና ሌሎቹን ባለሥልጣናት ገድሏል ተብሎ በመሪ ደረጃ ይጠረጠር የነበረውን የአማራ የደህንነት ቢሮ ሃላፊ ብርጋዴል ጄኔራል አሳምነው ጽጌን ገደሉ፡፡*

*ሃምሌ 11 የሲዳማ አክቲቪስቶች በተናጠል በወሰዱት ክልል የመመስረት ውሳኔ በሃዋሳ እና በአጠቃላይ በሲዳማ ዞን ውስጥ ሁከት ተፈጠሮ ይህንንም በመከተል በደርዘን የሚቆጠሩ ሰዎች ሞቱ፤ በብሄር ላይ*

የተመረኮዘ ጥቃት እንዲሁም የንብረት መውደም እና ሰፋ ያለ ዘረፋ ተካሄደ። ሃምሌ 11 እና ከዚያ በኋላ በደረሰ ረብሻ የሲዳማ ዞን ፓሊስ እንዳሳወቀው 53 ሰዎች ተገድለው 54 አካላቸው ላይ ጉዳት ደርሷል። የሞቱት ቁጥር የሚንፀባርቀው ከሆስፒታሎች በተገኘው መረጃ ላይ ተመርኩዞ ሲሆን በተለያዩ መንደሮች ተገለው የተቀበሩትን አያጠቃልልም፡፡ ይህንን አጋጣሚ በመከተል የሲዳማ ዞን በሚገኝበት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ያሉ ባለሥልጣናት የዕዝ ጣቢያ አቋቁመው ይህም ከመስከረም አንስቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የዕዝ ጣቢያው የደህንነት ጉዳዩን በፌዴራል ሃይሎች ሥር እንዲውል አድርጎታል፡፡

### ለ. መሰወር

በመንግሥት ባለሥልጣናት ወይም በነሱ ሥም የተፈጸሙ መሰወሮች ስለመኖራቸው ሪፓርት የተደረገ የለም።

ታህሳስ 24 የኦሮሞ ነፃነት ተዋጊዎች የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት የሆነውን ደሌሳ ቡልቻን ከምዕራብ ወለጋ ወደ አዲስ አበባ እየተጓዘ በነበረበት ወቅት ጠልፈው ነበር። ተዋጊዎቹ ከሦስት ቀናት በሏላ ለቀውታል።

በግንቦት ወር፤ የኦሮሞ ነፃነት ተዋጊዎች የኦሮሞ ዲሞክራቲክ ፓርቲ የሰዮ ወረዳ ሀላፊ የነበረውን ንጉሴ አቡን በምዕራብ ወለጋ ውስጥ ጠልፈው ገለውታል፡፡

### ሐ. ማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት

እንደዚህ አይነቶቹን እርምጃዎች ሕገ መንግሥቱ ይከለክላል፤ ቢሆንም ግን የደህንነት ባለሥልጣናት እስረኞች ላይ በደል እንደሚያደርሱ ሪፖርቶች ይሳያሉ፡፡

ሰኔ 15 ባህር ዳር እና አዲስ አበባ በተፈፀሙ ግድያዎች ሳቢያ፤ ከ300 በላይ አክትቪስቶችን፣ ፓለቲከኞችን እና ጋዜጠኞችን ፓሊስ በቁጥጥር ስር አውሎ ነበር። ፒያሳ በሚገኘው የአዲስ አበባ ፓሊስ ኮሚሽን ውስጥ ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ኢሰብዓዊ በሆነ መልኩ አቆያቸው እንዲሁም በተጨናነቀ፤ ቀዝቃዛ እና ጨለማ ክፍል ውስጥ አጉሮ በ 24 ሰዓታት አንድ ጊዜ ብቻ መጸዳጃ ክፍል እንዲጠቀሙ አደረገ። የሚዲያ ዘገባዎች እንደጠቆሙት የተጠርጣሪዎቹ ቤተሰብ እና ወዳጆች እንዲጎበኟቸው ፓሊስ አልፈቀደም። በምሽት ፓሊስ ተጠርጣሪዎቹን ለምርመራ እየጠራ ለብዙ ሰዓታት ቆመው እንዲቆዩ ያደርግ ነበር። የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ፤ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ፤ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ አባላት፤ ጋዜጠኞች እና ሲቪሎች መታሰራቸው እንዳሳሰበው የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ አሳውቋል፡፡

ሰኔ 27 እና 28፤ ተጠርጣሪዎች ናቸው የሚላቸውን ፓሊስ በመያዝ እና መጸዳጃ ቤት የሚጠቀሙበትን ጊዜ በጣም በመወሰን ቀዝቃዛ እና ጨለማ ክፍል ውስጥ አቆይቷቸዋል። እስረኞቹም ለጥቂት ቀናት የቆየ የረሃብ አድማ አደረጉ፤ እናም ሰኔ 29 የሽብር ድርጊት ፈጽመዋል ተብለው ፓሊስ ተጠርጣሪዎቹን ፍርድ ቤት አቀረበ፤ ከሰኔ 15 ግድያ ጋር ጉዳያቸውተያይዟል በማለት ተጠርጣሪዎቹ አዲስ አበባ ውስጥ ፓሊስ ጣቢያ በእስር እንዲቆዩ ሆኗል።

ሐምሌ 25 በዜና መግለጫ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒሥትር አብይ አህመድ መንግሥታቸው የሰብዓዊ መብት መከበር እንዲረጋገጥ እና የሕግ የበላይነት እንዲኖር እንደሚሻ ገልጸው ማሰቃየት እና እስረኞችን በጨለማ ማቆየት የሚለውን ሪፓርት ክደው ነበር፡፡

ሚያዝያ 2011 መንግሥት በአዲስ አበባ የሚገኘውና ባለፉት ዓመታት በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞበታል የሚባለው የፌደራል መንግሥት የምርመራ እና የእስር ተቋም መዘጋቱን አሳውቋል፡፡ የእስር

ቤት ሃላፊዎች ማዕከሉ ውስጥ ተይዘው የነበሩትን እስረኞች ወደ ሌላ ተቋም አዛውረዋል። ታህሳስ 2011 የፓርላማው የሕግ፤ የፍትህ፤ እና የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ቦታውን ጎብኝቶ መንግሥት ማዕከሉን እንደዘጋው አረጋግጧል። መስከረም 2011 በአሰቃቂ ሁኔታ እስረኞችን በማሰቃየት የሚታወቀውን የጅጅጋ ማዕከላዊ እስር ቤትን (የኡጋዴን እስር ቤት) የሱማሌ ክልል መንግሥት ዘግቶታል። ግንቦት 18 ጎረቤት ሶማሊያ ውስጥ የቀድሞውን የኡጋዴን እስር ቤት ሃላፊ ሃሳን ድህሬን የሶማሌ ክልል የደህንነት ባለሥልጣናት በቁጥጥር ስር አውለውታል፡፡

## እስር ቤት እና የማቆያ ማዕከል ሁኔታዎች

የእስር ቤት እና ቅድመ ክስ የማቆያ ቦታዎች ሁኔታዎች እጅግ አስቸጋሪ እና አንዳንዶቹ እንዲያውም ለሕይወት አስጊ ሆነው ታይተዋል፡፡ የጸጥታ ኃይሎች በማቆያዎች፣ በወታደራዊ ተቋማት እና በፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ በእስረኞች ላይ አካላዊ ጥቃት ማድረሳቸው ሪፖርት ተደርጓል፡፡ ካጋጠሙ ችግሮች መሃከል እስር ቤቶቹ ካላቸው የመያዝ አቅም በላይ በእስረኞች መጨናነቃቸው እንዲሁም በቂ ምግብ፣ ውሃ፣ ንጽሕናና የሕክምና እንክብካቤ አለመኖር ይጠቀሳሉ፡፡ ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት እስረኞች የሚቆዩባቸው የፖሊስ ጣቢያዎች ሁኔታ አንዱ ከሌላው እጅግ የተለየ መሆኑ፣ የንጽሕና ሁኔታ ዝቅተኛነት እና ፖሊሶች በእስረኞች ላይ የሚያደርሱት ጥቃት ተዘግበዋል፡፡

<u>አካላዊ ሁኔታዎች</u>፡- ከፍተኛ መጨናነቅ የተለመደ ነው፤ በተለይ በእስር ቤት የመኝታ ክፍሎች፡፡ ለምሳሌ በ2008 የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በሸዋ ሮቢት የሚገኘውን የፌደራል እስር ቤት ክፍሎች ጎብኝቶ፣ የክፍሉ ሁለት ትንንሽ መስኮቶች በግምት 40 ካሬ ሜትር (430 ካሬ ጫማ) ስፋት ላለው ክፍል አየር ለማስገባት በቂ አለመሆናቸውን ታዝበዋል እናም በዚህ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ 38 ታሳሪዎች ለእያንዳንዱ ሰው 1 ካሬ ሜትር (11 ካሬ ጫማ) ሂሰብ እጅግ አነስተኛ ነበር፡፡ የእስር ቤቱ ኃላፊዎች አንዳንድ ጊዜ ወጣት ጥፋተኞችን ከአዋቂዎች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ያስራሉ፡፡ የእስር ቤቱ አስተዳዳሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ወንዶችን እና ሴቶችን ለይተው የሚያስሩ ቢሆንም አንዳንድ ማዕከሎች ውስጥ መደባለቅ ተከስቷል፡፡

መንግሥት ለምግብ፣ ለውሃ እና ለጤና እንክብካቤ በቀን በግምት ዘጠኝ ብር ($0.31) የመደበ ሲሆን፣ ይህ የገንዘብ መጠን በአገሪቱ ዙሪያ ይለያያል፡፡ ከዓለም ባንክ በተገኘ መረጃ መሰረት የአገሪቱ አጠቃላይ የነፍስ ወከፍ ምርት በቀን አስራ ሁለት ብር ($0.41) ነው፡፡ በርካታ እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው በየዕለቱ ምግብ ስለሚቀርብላቸው ወይም በአካባቢው ካሉ የምግብ አገልግሎት ሰጪዎች ስለሚገዙ የመንግስትን አቅርቦት ይደግፋሉ፡፡ ሪፖርቶች እንደገለጹት የእስር ቤት ኃላፊዎች አንዳንድ እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው ምግብ እዳያገኙ ክልከላ ያደርጉባቸዋል። አንዳንድ ቤተሰቦች ዘመዶቻቸው የት እንደታሰሩም አያውቁም፡፡ ሕክምና በፌደራል እስር ቤቶች አስተማማኝ አይደለም፤ በክልል እስር ቤቶች ደግሞ ከሞላ ጎደል የማይታሰብ ነው፡፡ ለእስረኞች የንፁህ መጠጥ ውሃ ቅርቦት ከፍተኛ እጥረት አለ፡፡ የውሃ እጥረት የንጽህና ጉድለት እንዲንሰራፋ አድርጓል፤ አብዛኞቹ እስር ቤቶች ተገቢ የንጽሕና መስጫ ተቋማት የሏቸውም፡፡ ብዙዎች ታሳሪዎች ከፍተኛ የጤና ችግር እያለባቸው ያገኙት ሕክምና አነስተኛ ነው አሊያም ምንም ዓይነት ሕክምና አልተደረገላቸውም። የእስር ቤቱ ኃላፊዎች አንዳንድ እስረኞች ሕክምና እንዳያገኙ ከልክለዋል የሚሉም ሪፖርቶች አሉ፡፡

የፖለቲካ እስረኞች ጠያቂዎች እና ሌሎች ምንጮች እንደገለጹት የፖለቲካ እስረኞች ከሌሎች እስረኞች የተለየ አያያዝ ያጋጥማቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከቀረቡት አቤቱታዎች መሃከል ተገቢ ሕክምና እና መድኃኒት የማይገኝ መሆኑ፣ መጽሐፍት ወይም ቴሌቪዥን አለመኖሩ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዳይደረግ የሚጣል ክልከላ ይገኙባቸዋል፡፡

<u>አስተዳደር</u>፡- በሐምሌ 2010 የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በፌዴራል እስር ቤቶች የመብት ጥሰቶች ይፈጸማሉ ብሎ ባሰራጨው ዘገባዎች መነሻ መንግሥት አምስት የፌደራል ማረሚያ ቤቶችን ባለሥልጣናት አባሯል፡፡ በእስር ቤቶች የጥበቃ አባላት እንግልት የደረሰባቸው እስረኞች ያጋጠማቸውን እንግልት ለእስር ቤቱ አስተዳዳሪዎችም ሆነ ለእምባ ጠባቂ አካላት ለማሳወቅ እንዳይችሉ መደረጉ ተዘግቧል፡፡ በአንዳንድ እስር ቤቶች የሕግ እገዛ መስጫ ተቋማት አሉ፡፡ በክልል ደረጃ እነዚህ ተቋማት ከፍርድ ቤቶች፣ ከእስር ቤት እና ከሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣናት ወይም መሥሪያ ቤቶች ጋር ጥሩ የሥራ ግንኙነት አሏቸው፡፡ የእስር ቤት ኃላፊዎች ለአንዳንድ ታቃቢዎች ያለሳንሱር አቤቱታዎቻቸውን ለፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ ቢፈቅዱላቸውም፣ አንዳንድ ጊዜ ፍርድ ቤቶች እንዲህ ያሉትን አቤቱታዎች ለመስማት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀርተዋል።

ሕጉ እስረኞች እንዲጠየቁ ይፈቅዳል፡፡ ነገር ግን ባለሥልጣናት አንዳንድ ክስ የቀረበባቸው ተከሳሾች ከጠበቆቻቸው እና አባል ከሆኑባቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ጋር እንዳይገናኙ ክልከላ አድርገውባቸዋል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ፖሊሶች በምርመራ ላይ ያሉ እስረኞች ከቤተሰብ አባላት እና ከጠበቆቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ክልከላ አድርገዋል፡፡ የሀገሪቱ የእስር ቤት ደንቦች እንደሚሉት በሽብር ወንጀል የተከሰሱ ታሳሪዎች ጠበቆች በቀን መጠየቅ ወይም ማነጋገር የሚችሉት አንድ እስረኛ ብቻ ነው፤ ያውም በረቡዕ እና በዓርብ ቀናት ብቻ፡፡ የእስር ቤቱ ኃላፊዎች በሽብር ድርጊት የተከሰሱ ሰዎች ከቤተሰብ አባላት ጋር እንዳይገናኙ እገዳ ጥለዋል፡፡

የእስር ቤት ኃላፊዎች እስረኞች የኃይማኖት ሥርዓት እንዲፈጽሙ ቢፈቅዱም፣ ይህ ፈቃድ ግን ከአንድ እስር ቤት ወደ ሌላ እስር ቤት እንዲሁም በአንድ እስር ቤት ውስጥ እንኳን የአንዱ እስር ክፍል ከሌላው የተለየ ነው፡፡ የእስር ቤት ኃላፊዎች ታሳሪዎች የሚጸልዩበትን በቂ ቦታ ከልክለዋል የሚል አቤቱታ ቀርቧል፡፡

<u>ገለልተኛ ቁጥጥር</u>፡- ዓለም ዓቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (ICRC) የዓመታዊ መደበኛ ሥራው አካል በሆነ መልኩ በመላው አገሪቱ የሚገኙ ወህኒ ቤቶችን ጎብኝቷል፡፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በነበረበት ወቅት ኮሚቴው እስር ቤቶቹን ለመጎብኘት የነበረው ፈቃድ የተገደበ ነበር፡፡ ነገር ግን በሰኔ ወር አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሲነሳ፣ ዓለም ዓቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ ጉብኝቱን በብዛት ለማድረግ ችሏል፡፡ ሌሎች የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እስር ቤቶቹን እንዲጎበኙ መንግስት አልፈቀደም፡፡

የክልል ባለሥልጣናት ሦስተኛ ወገኖች በሌሉበት የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ከእስረኞች ጋር እንዲገናኙ ፈቅደዋል፡፡ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የፌዴራል እና የክልል እስር ቤቶችን ቃኝተዋል፣ እናም ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አለ በሚል ይቀርብ ስለነበረውም ክስ ከእስር ቤት አስተዳዳሪዎች እና ከእስረኞች ጋር ቃለ ምልልስ አድርገዋል፡፡ ጀስቲስ ፎር ኦል - ኢትዮጵያ ፕሪዘንስ ፌሎሺፕ (JPA-PFE) በአገሪቱ ዙሪያ የተለያዩ ማረሚያ ቤቶችን እና ማቆያ ተቋማትን ለመጎብኘት ችለዋል፡፡

### መ. በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል ወይም እስራት

ሕገ መንግሥቱ እና ሕጉ ሰዎች በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር እንዳይውሉ እና እንዳይታሰሩ ክልከላ ያደርጋሉ፤ እናም ማንኛውም ሰው በቁጥጥር ስር መዋሉን ወይም መታሰሩን ፍርድ ቤት ቀርቦ የመገዳደር መብት አለው። ይሁን እንጂ ባለሥልጣናት በዘፈቀደ ሰዎችን በቁጥጥር ስር ያውላሉ፤ አክቲቪስቶችን፣ ጋዜጠኞችን እና የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎችን ጨምሮ፡፡

ሰኔ 15 ባህር ዳር እና አዲስ አበባ ውስጥ ተቀነባብሮ የነበረውን ግድያ እንዲሁም ሓምሌ 11 ሲዳማ ዞን የደረሰውን ሁከት ተከትሎ የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት በሙቶ የሚቆጠሩ ተጠርጣሪዎችን ይዘው እና በቁጥጥር ስር አውለው ነበር። ሓምሌ 11 ገለልተኛው የመብት ቡድን አቀንቃኝ ኢሰመጉ ተቃዋሚ ቡድኖች

ላይ ያተኮረ እስርን በሚመለከት ሥጋቱን ገልጿል። ኢሰመጉ አስተያየት ሲሰጥ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ 102 አባላት እንዲሁም የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ እና የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ አባላት፣ ጋዜጠኞች እና ሌሎች ግለሰቦች በቁጥጥር ስር መዋላቸው የፓለቲካ ፓርቲዎቹ ላይ ጫና መፍጠሩ ብቻ ሳይሆን በአገሪቷ እየተካሄደ ያለውን ለውጥ ወደኋላ እንዲንሸራተት ያደርገዋል ብሏል።

በምዕራብ ኦሮሚያ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ታህሳስ 2011 የተቋቋመው የዕዝ ጣቢያ በሁለቱ ክልሎች ድንበር ላይ ደርሶ በነበረ ግጭት ሳቢያ ከተፈጠረው ሁከት፤ ሞት፤ እና የንብረት ጥፋት ጋር በተያያዘ 171 ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር እንዳዋለ አሳውቋል፡፡

## በቁጥጥር ስር የማዋል ሥርአቶች እና የታሳሪዎች አያያዝ

ሕገ መንግሥቱ እና ሌሎች ሕጎች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ ወይም እንደ አካባቢው ሁኔታ እና የመገናኛ ዘዴዎች በሚፈቅዱት መጠን ከተገለጸው ጊዜ ብዙም ሳይዘገይ ፍርድ ቤት ቀርበው ክስ እንደሚመሰረትባቸው ይደነግጋል፡፡ ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድ የሚወስደው ጊዜ በ48 ሰዓቱ ውስጥ አይካተትም፡፡ ከፍ ባለ የወንጀል ድርጊት ለተጠረጠሩ ሰዎች ምርመራ በመካሄድ ላይ እያለ ክስ ሳይመሰረት ለ14 ቀናት በእስር እንዲቆዩ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን፣ ይህ የ14 ቀናት ጊዜ በየወቅቱ ሊታደስ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቶችም ክስ ሳይመሰረት ምርመራዎች ከ14 ቀናት በላይ እንዲቀጥሉ ለደህንነት ኃላፊዎች ሲፈቅዱ ቆይተዋል፡፡

በጸረ-ሽበር አዋጅ ስር ፖሊስ ምርመራ እያካሄደ ሳለ ተጠርጣሪዎችን በ28 ቀናት ለተከፋፈሉ ጊዜያት ቢበዛ እስከ አራት ወራት ጊዜ ክስ ሳይመሰርት ጠይቆ በእስር ሊያቆይ ይችላል፡፡ ሕጉ "ጉልህ ወንጀሎች" በሚፈጸሙ ጊዜ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማሰርን ይፈቅዳል፡፡ እነዚህ ወንጀሎችን ሲፈጽሙ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ወይም ወንጀል ለመፈጸም በመሞከር ላይ ያሉ ወይም ወንጀሉን እንደፈጸሙ ወዲያውኑ የተደረሰባቸው ተጠርጣሪዎችን ያካትታል፡፡

በይፋ በሚታወቁ ተቋማት ካልሆነ በቀር እስረኞችን ማሰር የተከለከለ መሆኑ በሕጉ ተደንግጓል፤ ሆኖም ግን የአካባቢ ታጣቂዎች እና ሌሎች መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ ሕግ አስከባሪ አካላት ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ይፋዊ ያልሆኑ የእስር ማዕከላት ነበሯቸው፡፡

ውጤታማ የዋስትና ሥርዓት ተግባራዊ ተደርጎ ነበር፡፡ በሽብር ወንጀል፣ በግድያ፣ በአገር ክህደት እና በሙስና ወንጀሎች ክስ ለተመሰረተባቸው ሰዎች ዋስትና የለም፡፡ በሌሎች ጉዳዮች ደግሞ ፍርድ ቤቶች ከብር 500 እስከ ብር 10,000 ($17 and $346) የዋስትና ገንዘብ የሚወስኑ ቢሆንም፣ አብዛኞዎቹ የአገሪቱ ዜጎች ይህንን ያህሉን የዋስትና ገንዘብ መክፍል የሚችሉ አይደሉም፡፡ በግል ጠበቃ ማቆም ለማይችሉ ተከሳሾች መንግሥት ጠበቃ ያቆምላቸዋል፤ ሆኖም ግን ተከሳሾች እንዲህ ያለውን አገልግሎት የሚያገኙት ጉዳዮቻቸው ወደ ፍርድ ቤት ሲሄዱ እንጂ ወሳኝ በሆነው ቅድመ የፍርድ ሂደት ወቅት አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአንድ ጉዳይ ለበርካታ ተከሳሾች አንድ ጠበቃ ሲቆም ታይቷል፡፡ አንዳንድ ታሳሪዎች በምርመራ ላይ እያሉ በእስር ላይ ቢገኙም፣ ከሕግ አማካሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በባለስልጣናት የተገደበ እንዲሆን ወይም ጭራሹንም እንዳይገናኙ መደረጉ፣ ስለጤናቸው ሁኔታ ሙሉ መረጃ አለመሰጠቱ፣ በቤተሰቦቻቸው እንዲገበኙ አለመፈቀዱም በሪፖርቶች ቀርቧል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የእስር ቤት ኃላፊዎች እስረኞችን ከሌሎች ለይተው ብቻቸውን ለዛምንታት አስረው እንደሚያቆዩ፤ እንዲሁም ሲቪል ሰዎችን ይፋ ላልተደረገ ጊዜ የቁም እስረኛ እንደሚያደርጉ ተዘግቧል፡፡

<u>በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል</u>፡- ባለሥልጣናት የተቃውሞ ሰልፈኞችን፣ ጋዜጠኞችን እና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ሲያስሩ ቆይተዋል፡፡ የጸጥታ ኃይሎች ሰዎችን በዘፈቀደ ስለማሰራቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ሪፖርቶች አሉ፡፡

ሐምሌ 4 የደህንነት ባለሥልጣናት የአማራ ፓለቲካ ንቅናቄ ፓለቲካ ፓርቲ አፈ ቀላጤ የሆነውን ክርስቲያን ታደለን በአዲስ አበባ ውስጥ የታሰሩ የድርጅትን አባላት በመጎብኘት ላይ እንዳለ በቁጥጥር ስር አዋሉት። ነሃሴ 3 ፓሊስ ክርስቲያንን የሽብር ወንጀል ፈጽሟል ብሎ እንደሚጠረጥረው ለፍርድ ቤት አሳወቀ። ሰኔ 15 ባህር ዳር እና አዲስ አበባ ውስጥ የተፈጸመውን ግድያ ተከትሎ የአማራ ፓለቲካ ንቅናቄ የመንግሥት የደህንነት ሃይሎች ከ500 በላይ አባሎቼን በስፋት አስሮብኛል ብሏል። ይህም ሃምሌ 19 ሪፓርት የተደረገውን የበለጠ ካሳን የአማራ ፓለቲካ ንቅናቄ ዋና ጸሃፊን፤ የአንተነህ ስለሺን የፓለቲካ ጉዳይ ሃላፊን፤ የወጣቶች ጉዳይ ሃላፊውን የንጉሴ ይልቃልን እስራት ጨምሮ ነው። በነሃሴ ውስጥ አነግ ቁጥራቸው ያልታወቀ አባሎቼ እና ደጋፊዎቼ ኦሮሚያ ውስጥ ታስረውብኛል፤ ጥቂቶቹ የተለቀቁትም “የፓለቲካ ዳግም ሥልጠና” ውስጥ ካለፉ በኋላ ነው ብሏል፡፡

የአዲስ አበባ ፓሊስ መስከረም 2012 ውስጥ አነግ ወደ ቡራዩ ተመለስኩ ካለ በኋላ በተከሰተው ሁከት እንጠረጥራቸዋለን ያሏቸውን 1,204 ወጣቶችን በቁጥጥር ስር አውሏል። ጦላይ የጦር ማሠልጠኛ ሰፈር ውስጥ ይዟቸው ወር የሚሞላ “የንቃት ትምህርት” ሰጥቻቸዋለሁ ይላል። ፓሊስ ጥቅምት 7 1,174 እስረኞችን የፈታ ሲሆን ዓመቱ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ የቀሩት 30 ወጣቶች ሁኔታ ምን ላይ እንዳለ መንግሥት አላሳወቀንም፡፡

<u>የቅድመ ፍርድ ሂደት/የምርመራ ጊዜ እስር</u>፡- አንዳንድ ታሳሪዎች ክስ ሳይመሰረትባቸው ወይም ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለዓመታት በእስር ላይ መቆየታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በእስር ላይ የቆዩ ታሳሪዎች ብዛት በመቶኛ እና አማካይ የእስር ጊዜያቸውን የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ ረጅም ጊዜ የፈጀ የክስ ሂደት፣ ከፍተኛ የታሳሪዎች ቁጥር፣ የፍርድ አካላት አቅም አናሳ መሆን እና የባለሙያዎች እጥረት የፍርድ ቤት ጉዳዮች እንዲጓተቱ፣ አንዳንድ ጊዜም ለዓመታት እልባት ሳያገኙ እንዲቆዩ ምክንያት ይሆናሉ።

<u>በቁጥጥር ስር የዋለ ቁጥጥር ስር መዋሉ ሕጋዊነትን በሚመለከት ከፍርድ ቤት ፊት ቀርቦ መገዳደር፤</u> በጥፋት የተከሰሰ ወይም የተወነጀለ ግለሰብ ይግባኝ የማለት መብቱን ሕጉ ዕውቅና ይሰጣል፤ ግለሰቡ ሕገወጥ ቁጥጥር ስር ውያለሁ ሲል በዚህ ዓመት ውስጥ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ስለመኖሩ መዝገቡ የሚያሳየን የለም፤ በሕገወጥ መልኩ ለተያዙ ግለሰቦች የወንጀል ሕጉ ካሳ አይከፍልም፡፡

### ሠ. በፍትሐዊ ክፍት ችሎት የመዳኘት መብትን መከልከል

ሕጉ ፍርድ ቤቶች ገለልተኛ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ የፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው በገለልተኝነት የሚሰሩ ቢሆኑም፣ የወንጀል ፍርድ ቤቶች ግን ደካማ፣ በሥራ ጫና የተጨናነቁ እና የፖለቲካ ጫና የሚደርስባቸው ናቸው፡፡

### የፍርድ ስራዓቶች

በሕገ መንግሥቱ መሠረት ክስ የቀረበባቸው ሰዎች በክፍት ችሎት በፍትሐዊ የፍርድ ሂደት ውሳኔ የማግኘት መብት ስላላቸው፣ የፍርድ ሂደቱም ተገቢ ካልሆነ በመዘግየቱ ምክንያት ነጻ የመሆን፣ ተከሳሾች ነጻ ተደርገው የመቆጠር መብት፣ በራሳቸው ምርጫ ጠበቃ የማቆም፣ ይግባኝ የመጠየቅ፣ በራሳቸው ላይ ያለመመስከር መብት፣ ምሥክሮች እና የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ እንዲሁም ለዓቃቤ ሕግ ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡ በሕጉ እንደተቀመጠው ተከሳሾች በሚረዱት ቋንቋ የፍርድ ሂደቱን

እንዲከታተሉ አስተርጓሚ መመደብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ለዋና ዋና ቋንቋዎች አስተርጓሚዎች አሏቸው፤ ሌሎች ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ተከሳሾች ደግሞ አስተርጓሚዎች እንዲቀጥሩ ሕጉ ያዛል፡፡

ለታሳሪዎች እነዚህ መብቶች ሁሉ ተከብረውላቸዋል ማለት አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት አንዳንድ ጊዜ መከላከያ ጠበቆች በቂ ክርክር ለማቅረብ ሳይዘጋጁ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች ሁል ጊዜ ተከሳሾችን ነጻ አድርገው አያዩም፤ ተከሳሾች የራሳቸውን ጠበቃ እንዲቀጥሩ አይፈቅዱም፤ ጊዜውን የጠበቀ መከላከያ አያቀርቡም ወይም በመንግሥት ዘንድ የሚገኙ ማስረጃዎች እንዳይቀርቡ ክልከላ ያደርጋሉ፡፡ ተሰካሾች ብዙ ጊዜ የፍርድ ሂደት እስኪጀመር ድረስ በተለይ የተከሰሱበትን ጉዳይ አያውቁም፡፡ ኃላፊዎች ከታሳሪዎች መረጃ ለማግኘት ወይም የተከሳሽነት ቃል ለመቀበል ሲሉ የኃይል ድርጊት ስለመፈጸማቸው ያልተረጋገጡ ዘገባዎች ቀርበዋል።

የፌደራል መንግሥት የተከላካይ ጠበቆች መሥሪያ ቤት ለምስኪን ተከሳሾች የሕግ ምክር አገልግሎት የሰጠ ሲሆን፣ በጠበቆች እጥረት ምክንያት የአገልግሎቱ ስፋት እና ጥራት ግን በቂ አይደለም፡፡ አንድ በመንግሥት ተቀጥሮ ለተከሳሾች አገልግሎት የሚሰጥ ጠበቃ ከ100 በላይ ጉዳዮችን የሚይዝ በመሆኑ፣ ለአንድ ጉዳይ በርካታ ተከሳሾችን ሊወክል ይችላል፡፡ በርካታ ነጻ የሕግ አገልግሎት መስጫዎች በተለይ ደግሞ በዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ሆነው የሕግ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ ለምሳሌ የሕግ ተማሪዎች እና የሕግ መምህራን ያለክፍያ የሕግ አገልግሎት እንዲሰጡ ሕጉ ይፈቅድላቸዋል፡፡ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ወይም ሌላ ደረጃ የወጣለት የወንጀል ጥብቅና ደንብ ግን የለም፡፡

በሕገ መንግሥቱ ኃይማኖታዊ እና ባሕላዊ የፍርድ ሥርዓቶች ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ በርካታ ዜጎች ለመደበኛ የፍርድ ሥርዓቶች ያላቸው ተደራሽነት የተገደበ ሲሆን፣ አለመግባባቶችን ለመፍታት በአብዛኛው የሚተማመኑት በባሕላዊ የፍርድ አካሄዶች ነው፡፡ በሕጉ እንደተቀመጠው አለመግባባት ላይ ያሉ ወገኖች ጉዳያቸው በባሕላዊ ወይም በኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት እንዲታይላቸው መጀመሪያ መስማማት አለባቸው፤ አንዱ ተከራካሪ ወገን ግን በማንኛውም ጊዜ በመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የሸሪዓ (እስላማዊ) ፍርድ ቤቶች ኃይማኖታዊ እና የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ያሉባቸውን የቤተሰብ ጉዳዮች ያያሉ፤ ይህም የሚሆነው ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኞች ከሆኑ ነው፡፡ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከመንግሥት የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡ እነዚህ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የእስልምና ተከታይ በሚበዛባቸው በሶማሌ እና አፋር ክልሎች በበርካታ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ሌሎች ባሕላዊ ሥርዓቶች፣ ለምሳሌ የአገር ሽማግሌዎች በተለይ በገጠር አካባቢዎች አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ አንዳንድ ሴቶች በባሕላዊ የፍርድ አሰጣጥ ሥርዓቶች ነጻ እና ፍትሐዊ ዕድል እንዳልተሰጣቸው ይናገራሉ፤ ምክንያቱም የአካባቢው ባሕል በሽምግልና ጉባዔው እንዳይሳተፉ ስሚከለክላቸው እና አሁንም ድረስ ሊቀረፍ ያልቻለ የጾታ መድልዖ ያለ በመሆኑ ነው፡፡

## የፖለቲካ እስረኞች እና ታቃቢዎች

የአዲስ አበባ ፓሊስ ፍሬው በቀለን፣ የሪፍት ቫሊ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰርን ዘ ሃይጃከድ ሪቮሊሽን (የተጠለፈው አብዮት) በሚል ርዕስ መጽሃፍ ስለጻፈ በጸረ ሽብርተኛ ክስ ወንጅሎት በቁጥጥር ስር አውሎ መጽሃፉ የጠቅላይ ሚኒሥትር አብይን አስተዳደር በከፍተኛ ደረጃ ይወቅሳል፣ ጠቅላይ ሚኒሥትር አብይ የኦሮሞን ጉዳይ መወከል አቁመዋል ሲል።ፓሊስ አዲስ አበባ ውስጥ ካሉ መጽሃፍ ቸርቻሪዎች ላይ መጽሃፋቸውን

ነጥቋል፣ የመጽሃፍ መደብር የነበራቸው ሶስት ወንድማማቾችም ታስረዋል። እስከ ጥቅምት ድረስ ፓሊስ ፍሬውን እና ከሶስቱ ሁለቱን ወንድማማቾች በቁጥጥር ላይ እንዳሉ አቆይቷቸዋል፡፡

የአገር ውስጥ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ሪፓርት እንዳደረጉት ፓሊስ በፓለቲካ ምክንያት ከ 200 በላይ ግለሰቦችን እና ቁጥራቸው 2000 የሚጠጋ ግለሰቦችን በጅምላ በተለያዩ ጊዚያት በቁጥጥር ስር አውሏል ይላሉ። መንግሥት በበኩሉ እነዚህ እስረኞች በቁጥጥር ስር የዋሉት በወንጀል ተከሰው እንጂ በፓለቲካ አይደለም ይላል፡፡

<u>ይቅርታ፤</u> ጠቅላይ ሚኒሥትር አብይ የፓለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በጠየቁት መሰረት፤ ፓርላማ ከሃምሌ 13፤ 2011 ጀምሮ እስከ ጥር 12 ድረስ የቆየ የይቅርታ ሕግ አጸደቀ። 13200 ግለሰቦች በይቅርታው ሕግ የተፈቱ መሆናቸውን የፌዴራል ዓቃቢ ሕግ አሳውቋል። በፓሊስ ምርመራ ላይ ያሉ፤ ችሎት ለመቅረብ እየተጠባበቁ ያሉ፤ ወይም በፓለቲካ ወንጀል የተፈረደባቸው፤ አገር በመካድ፤ ሕገ መንግሥቱን በመዳፈር፤ እና የትጥቅ ትግል በማካሄድ አይነት ወንጀሎች የተከሰሱ ግለሰቦች ይቅርታ ተደርጎላቸዋል፡፡ ዘር በማጥፋት የተፈረደባቸው፤ ከሕግ ውጪ ግድያ የፈጸሙ፤ ሃይል ተጠቅመው ጠለፋ ወንጀል የፈጸሙ፤ እና የማሰቃየት ወንጀል የፈጸሙ ለይቅርታው ብቁ አልሆኑም፡፡

## የፍትሐ ብሔር ስርዓቶች እና መፍትሔዎች

ዜጎች አቤቱታቸውን ለፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ያላቸው ሲሆን፣ አቤቱታ ሊያቀርቡባቸው የሚችሏቸው ጉዳዮች የሰብዓዊ መብት ጥሰትን እንደሚጨምሩ ይደነግጋል፡፡ የሰብዓዊ መብትን ጥሷል የተባለው አካል የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ ተጠቂው ሰው አቤቱታውን መጀመሪያ ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ያቀርባል፡፡ ፓርላማው የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንን ያቋቋመው በ 1992 ሲሆን፣ ለኮሚሽኑ ገንዘብ ሲመድብ እና ሥራውንም ሲከታተል ቆይቷል፡፡ ኮሚሽኑ ጉዳዮችን ከመረመረ በኋላ ለሚመለከተው የመንግሥት ኤጀንሲ የውሳኔ ሃሳቡን ያቀርባል፡፡ ዜጎች ማስረጃ ማግኘት ባለመቻላቸው፣ አለበለዚያም ይህ ተቋም እንዲህ ባሉት ጉዳዮች ላይ ከመድልዖ ነጻ የሆነ ውሳኔ ሊሰጠን አይችልም በሚል እምነት ማጣት ለተቋሙ አቤቱታ አላቀረቡም፡፡

የዳንኤል በቀለን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽነርነት ሹመት ፓርላማ ሰኔ 25 አፅድቋል። ዳነኤልም በይፋ “ትርጉም ያለው ለውጥ” የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽነር እንደሚያስፈልገው እና የመንግሥት ጸረ ሽብርተኛ ድንጋጌን መጠቀም መቀጠሉን በመቃወም ከመንግሥት ጫና ነፃ መሆኑን ከጅምሩ አመልክቷል፡፡

## ረ. በግል ሕይወት፣ በቤቴሰብ፣ በመኖሪያ ቤት ወይም በደብዳቤ ልውውጥ ላይ በዘፈቀደ ወይም በሕገ ወጥ ሁኔታ ጣልቃ መግባት

በግል ንብረት ላይ ፍተሻ ከማካሔድ አስቀድሞ ባለስልጣናት የፍርድ ቤት ማዘዣ ማግኘት እንዳለአቸው ሕጉ ይደነግጋል፡፡ አፋጣኝ ክትትል በሚያስፈልግበት ወቅት ተጠርጣሪ አንዳንድ ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ቢገባ ወይም ጥፋት የተፈጸመባቸውን ቁሳቁሶች ከቅጥር ገቢዎቹ ቢያስወግድ ህጉ ለየት ላሉ ሁኔታዎች እውቅና ይሰጣል። በዚህ ለየት ላለ ሁኔታ የፖሊስ አባላት በዚያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሦስት ዓመት በላይ የእስር ቅጣት ሊያስከትል የሚችል ወንጀል ማስረጃ በዚያ ገቢ ውስጥ ተደብቋል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖራቸው ወይም የፍተሻ ትዕዛዝ ከፍርድ ቤት ማግኘት ጊዜ ስለሚፈጅ እና በዚያ ጊዜ ውስጥ ማስረጃው ከዚያ ስፍራ ሊወሰድ ይችላል ብለው ካመኑ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፍተሻ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ሌላ የጸረ ሽብር አዋጅ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባይኖር እንኳን የግለሰቦች ቤቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ሊፈተሹ እንደሚችሉ፣ አንዲህ ላለው ብርበራ የፌደራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ወይም በእርሳቸው የተወከለ ሰው

ወይም የሽብር ድርጊት ሊጸፈም ስለሚችል ድንገተኛ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነ ፖሊስ መፍቀድ እንዳለበት ሕግ ይደነግጋል፡፡

ባለሥልጣናት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ከሥራቸው እንዳባረሯቸው እና ከኢሕአዴግ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ነዋሪዎች ሥራ ለማግኘት ከቀበሌዎቻቸው መስጠት የሚገባቸውን "የድጋፍ ደብዳቤ" ማግኘት አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው (በክፍል 3፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የፖለቲካ ተሳትፎ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) ዘገባዎች ያመለክታሉ፡፡

**ክፍል 2. የሲቪል መብቶችን ማክበር፣ ከእነርሱም መካከል፡-**

***ሀ. ፕሬስን ጨምሮ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣***

ሕገ መንግሥቱ እና ሕግ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ እና የፕሬስ መብትን ያከብራሉ። በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በተሰጠ ማበረታቻ፣ በርካታ አዳዲስ እና የተመላሽ ዳያስፖራ ሚዲያዎች በአገሪቱ መመዝገብ እና መሥራት ችለዋል።

ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት፡- ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በመጋቢት 2011 ወደ ሥልጣን ሲመጡ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ለወደፊቱ ለአገሪቱ እጅግ ተፈላጊ ነው ብለው ነበር፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አከታትለው እንደገለጹት መንግሥት ላይ ሂስ የሚያቀርቡ ሰዎችን በቁጥጥር ስር ማዋል፣ ማሰር፣ ጥቃት ማድረስ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፡፡

የፕሬስ እና የድረ ገጽ ሚዲያን ጨምሮ የሚዲያ ነጻነት፡- ገለልተኛ ሚዲያዎች በግላቸው በተመጣጣኝ ዋጋ ገለልተኛ ማተሚያ ቤት ለማግኘት ያላቸው ዕድል በአንድ በመንግሥት ባለቤትነት ስር ባለ ማተሚያ ድርጅት የተገደበ ነው፡፡ በዚህም ረገድ መንግሥት ያስፈራራል፡፡ ገለልተኛ የዜና ማሰራጫዎች እንዳሉት የሕትመት ሚዲያ ቁጥር ማነስ፣ ዝቅተኛ ስርጭት እና የሕትመት መዛባት ዋነኛ ምክንያት የማተሚያ ተቋም እጥረት መሆኑን ገልጸዋል። በዚህ ዓመት የመንግሥት ሚዲያ ሚዛናዊ የሆነ ሪፓርት የማድረግ አዝማሚያ አሳይቷል፤ ቢሆንም ግን ጠንካራ የመንግሥት ጫና እንዳለ ግልጽ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ውስጥ ስድስት ገለልተኛ ጋዜጦች በድምሩ በሳምንት የ44,000 ቅጂዎች ስርጭት ነበራቸው፤ በተጨማሪ ሁለት በስፖርት ላይ ያተኮሩ ጋዜጦች ነበሩ፡፡ ከዋና ከተማዋ ውጪ ገለልተኛ ጋዜጦች አልነበሩም፡፡ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተሙ ስምንት ገለልተኛ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ ጋዜጦች እና በወር ሁለት ጊዜ የሚታተሙ መጽሄቶች በድምሩ የ27,000 ቅጂዎች ስርጭት ነበራቸው፡፡ በመንግሥት ባለቤትነት ስር ያሉ ጋዜጦች ደግሞ በድምሩ በቀን የ50,000 ቅጂ ስርጭት ነበራቸው፡፡ አብዛኞቹ ጋዜጦች የሚታተሙት በሳምንት ወይም በሁለት ሳምንት ጊዜ ሲሆን፣ በመንግሥት የሚታተሙ ጋዜጦች እና አንድ ዴይሊ ሞኒተር የተባለ የግል ጋዜጣ ደግሞ ዕለታዊ ነበሩ፡፡ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉ ሚዲያዎች የመንግሥትን እና የገዢውን ፓርቲ የኢሕአዴግን አቋሞች በቅርበት ያንጸባርቃሉ፡፡ በብሔራዊ ደረጃ ስርጭት ያለውን ቴሌቪዥን እና ሬዲዮ የሚቆጣጠረው መንግሥት ሲሆን፣ እርሱም ለአብዛኛው የአገሪቱ ዜጋ ብቸኛው የዜና ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ መላውን አገሪቱን የሚሸፍኑ ሁለት የመንግሥት የሬዲዮ ጣቢያዎች ያሉ ሲሆን፣ 12 የኤፍኤም የግል ሬዲዮ ጣቢያዎች በዋና ከተማዋ ውስጥ ያሰራጫሉ፤ በትግራይ ክልል አንድ FM ሬዲዮ እና በሌሎች ክልሎች ደግሞ 49 የማኅበረሰብ ሬዲዮ ተቋማት ያሰራጫሉ፡፡ የመንግሥት አካል የሆነው የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በአገሪቱ ከፍተኛ ስርጭት ያለው ሲሆን፣ ከእርሱ በመቀጠል ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሰፊ የስርጭት ሽፋን አለው፤ ፋና ከገዢው የኢሕደግ ፓርቲ ጋር ቁርኝት አለው ይባላል፡፡ ፈቃድ የተሰጥቸው 31 የሳተላይት ቴሌቪዥን እና 28 ሬዲዮ ጣቢያዎች አሉ።

የፖለቲካ እና የኃይማኖት ድርጅቶች እንዲሁም የውጭ አገር ዜናች የብሮድካስት ጣቢያዎች ባለቤቶች እንዲሆኑ ሕጉ አይፈቅድም፡፡

ሁከት እና ማሳደድ፡- መንግሥት በጋዜጠኞች ላይ ሲፈጽም የነበረው በቁጥጥር ስር የማዋል ተግባር፣ ጥቃት እና ክስ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሱ ሲሆን ታስረው የነበሩ ጋዜጠኞች ተፈተዋል።

የካቲት 16 ባለቤትነቱ የግል ከሆነው መረጃ ቴሌቪዥን ሁለት ጋዜጠኞች በኦሮሚያ ክልል ፓሊስ ቁጥጥር ስር ውለው ነበር። በቁጥጥር ስር በዋሉ ጊዜ ሪፓርተር ፋሲል አረጋይ እና የካሜራ ባለሙያ ሃብታሙ ኦዳ በቤቶቻቸው መደምሰስ ምክንያት የተፈናቀሉ ግለሰቦችን ቃለመጠይቅ እያደረጉ ነበር፤ በቁጥጥር ስር ከዋሉም በኋላ በለገጣፎ ፓሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት የአመጽ ቡድን ሁለቱን ጋዜጠኞች አጥቅተዋል፡፡

ሐምሌ 11 የደህንነት ሠራተኞች በሃዋሳ የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ዋና ከተማ ውስጥ የሲዳማ ሚዲያ ኔትዎርክ አስተዳዳሪ የሆኑትን ጌታሁን ደጉዬ እና ታሪኩ ለማን እንዲሁም ሁለት የቦርድ አባላትን አስረዋል፤ አንደኛውን የቦርድ አባል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፓሊስ ሲለቀው ሌሎቹን ግን ሐምሌ 11 ሲዳማ ዞን በተከሰተው ሁከት ውስጥ ተሳትፋችኋል በማለት በቁጥጥር ስር አቆይቷቸዋል፡፡

በሳንሱር እና በይዘት ላይ ስለሚደረግ ገደብ፡- በርካታ የግል ጋዜጦች በመንግሥት መደበኛ ያልሆነ ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው ገልጸዋል፡፡ መንግሥት ከሚያደርጋቸው ጣልቃ ገብነቶች መካከል እንደ ምሳሌ የሚጠቀሰው አንዳንድ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና መንግስትን የሚተቹ ናቸው የሚባሉ ጉዳዮችን አስመልክቶ ከመንግሥት ባለሥልጣናት የስልክ ጥሪ መደረጉ በዚህ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ የግሉ ዘርፍ እና የመንግሥት ጋዜጠኞች በየእለቱ ራሳቸውን ሳንሱር ያደርጋሉ፡፡

**የኢንተርኔት ነጻነት**

መንግስት በየጊዜው ኢንተርኔትን ሲገድብ እና ሲያቋርጥ ቆይቷል። የተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያ ድረ ገጾችም የተዘጉባቸው ወቅቶች ነበሩ፡፡ ከሰኔ 3 ጀምሮ ባልታወቁ ምክንያቶች መንግሥት በከፊል እና ቀጥሎም ሙሉ ለሙሉ ኢንተርኔትን ለሳምንት አቋርጦ ቆየቷል። ብዙዎች ከብሔራዊ ትምህርት ቤት መልቀቂያ ፈተና ጋር ይገናኛል ይላሉ፤ መንግሥት በ2011 ማወክ ያቆመላቸውን ብሎጎች እና የተቃዋሚ ድረ ገጾችን ኢትዮጵያዊያን ማግኘታቸውን ቀጥለዋል። ሴኔ 15 ባህር ዳር እና አዲስ አበባ ውስጥ የተከሰተውን ግድያ ተከትሎ መንግሥት ኢንተርኔቱን አቋርጦል። የማህበራዊ ሚዲያዎችን እንደ ፌስቡክ እና ትዊተር ያሉትን እያቋረጠ በከፊል የኢንተርኔት ግንኙነት እንዲቀጥል አድርጓል፡፡

በአገር ውስጥ ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ባለቤትነቱ የመንግሥት የሆነው ኢትዮ ቴሌኮም ብቻ ነው፡፡

የኮምፒዩተር ወንጀሎችን የሚመለከተው ሕግ ከመጠን በላይ ሰፊ አንቀጾችን የያዘ ሲሆን እነዚህም የመናገር እና እራስን የመግለጽን ነፃነት ሊገድቡ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል አንደኛው አንቀጽ ኮምፒዩተርን በመጠቀም በጽሁፍ፣በቪዲዮ፣ በድምጽ ወይም በማንኛቸውም ምስሎች ታግዞ ለአመጽ ማነሳሳት፣ ረብሻ መፍጠር ወይም በግለሰቦች መሃከል ግጭት የሚፈጥሩ መረጃዎች በእስር ያስቀጣሉ ይላል፡፡

ተጠቃሚዎች ከመንግሥት ክትትል ውጪ ሆነው በኢንተርኔት እና በኢሜል ለመጠቀም የሚያስችላቸውን መዳረሻ ቨርቹዋል ፕራይቬት ኔትወርክን ባለሥልጣኖች በአገልግሎት ሰጪዎቹ ላይ ዘጉባቸው፡፡ በመስከረም

ወር Axios.com የሚባለው ድረ ገጽ እንደዘገበው መንግሥት የኮምፒዩተር የስለላ ዘዴን በመጠቀም ጋዜጠኞችን ይከታተላል፡፡

## አካዳሚያዊ ነጻነት እና ባሕላዊ ክስተቶች

መንግሥት አካዳሚያዊ ነጻነትን በቀዳሚነት ተቆጣጣሪ መምህራንን በማሰማራት እና በሥርዓተ ትምህርት አማካኝነት ገድቧል፡፡ ባለሥልጣናት በተደጋጋሚ በዩኒቨርሲቲ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የንግግር እና ሃሳብን የመግለጽ መብት ላይ ገደብ ይጥላሉ፡፡

በበርካታ ሪፖርቶች ላይ እንደተገለጸው፣ ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ለገዢው ፓርቲ ድጋፍ ያላቸውን ተማሪዎች ለድህረ ምረቃ ዲግሪ እንዲመረጡ ማድረጉን ቀጥሎበታል፡፡ እንደ አንዳንድ የዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች ግንዛቤ የፓርቲ አባል የሆኑ ተማሪዎች ከምረቃ በኋላ በሁሉም መስኮች ቅድሚያ የቅጥር ዕድል እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ የተለያዩ ተጨባጭ ሪፖርቶች እንዳሳዩት የኢሕአዴግ አባል ያልሆኑ መምህራን በቂ ዕድገት እና የሙያ ማሻሻያ ዕድል አያገኙም ነበር፡፡ በአካዳሚያዊ ሠራተኞች ላይ በሚወሰዱ ውሳኔዎች ላይ ግልጽነት ይጎድል ስለነበር ከፓርቲ ጋር ባለ ግንኙነት፣ በብሔር ወይም በኃይማኖት ላይ ተመስርቶ መድልዖ እንደሚደረግ ብዙ ቅሬታዎች ይቀርቡ ነበር፡፡

የተለየ የትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ የግል ዩኒርሲቲዎች የሕግ እና የመምሕራን ትምህርት እንዳያስተምሩ ክልከላ ያደርጋል፡፡ ከዚህም ሌላ መመሪያው የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ሥርዓተ ትምህርታቸውን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሳይንስ እና ማኅበራዊ ሳይንስ የ70/30 ንጽጽር ጋር እንዲያጣጥሙ ያስገድዳል፡፡ በዚህም ምክንያት ማኅበራዊ ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት እየቀነሰ ሄዷል፤ በሌላ በኩል የግል ዩኒቨርሲቲዎች በይበልጥ ያተኮሩት በማኅበራዊ ሳይንስ ላይ ነበር፡፡

በሪፖርቶች መሠረት ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፎችን ያደርጉ ይሆናል በሚል አስቀድሞ በተለይ በኦሮሚያ በሚገኙ ዩነቨርሲቲ ቅጥር ግቢዎች የደንብ ልብስ እና የአዘቦት ልብስ የለበሱ የጸጥታ ኃይል አባላት በከፍተኛ ቁጥር እንዲጨምሩ ተደርጓል፡፡

## ለ. የሰላማዊ ስብሰባ እና የመደራጀት ነፃነት

መንግስት በሰላማዊ ስብሰባ እና በመደራጀት መብት ላይ ገደቦች ጥሎ ነበር፡፡

### በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት

ህገ መንግስቱና ህጉ በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት መኖሩን ይደነግጋሉ። ሆኖም መጋቢት 15 በግንቦት 7 የተደራጀ የከተማ ነዋሪዎች ስብሰባ ባህር ዳር ከተማ ውስጥ በወጣት ቡድኖች ተቋረጠ። የደረሰን ሪፖርት እንዲሚጠቁመው ወጣቶቹ ሃይል በመጠቀም ወደ ስብሰባው አዳራሽ ከገቡ በኋላ የድርጅቱን መፈክሮች በማውረድ በራሳቸው መልዕክቶች ቀይረዋል። የመንግሥት የደህንነት ሃይሎች ወጣቶቹን አልከለከሏቸውም።

ባለስልጣናት ፈቃድ መስጠትን መከልከል ባይችሉም ለህዝብ ደህንነት ወይም ለመዘዋወር ነጻነት ሲባል ቦታው ወይም ጊዜው/ሰዓቱ እንዲለወጥ ማድረግ ችለዋል፡፡ አንድ ዝግጅት ወደ ሌላ ቦታ ወይም ጊዜ/ሰዓት እንዲለወጥ ባለስልጣናት ካሳሰቡ፣ በህጉ መሰረት ባለስልጣናቱ ጥያቄው በቀረበ በ12 ሰዓታት ውስጥ ለአዘጋጆቹ በጽሑፍ ማስታወቅ አለባቸው፡፡

ኢሕአዲግ ለስብሰባዎችና ለዝግጅቶች በአዲስ አበባ፣ በክልል ከተማች እና በመንግስት ድርጅቶች ውስጥ ባሉ የራሱ የጉባኤ ማዕከላት ተጠቅሟል።

በአክትቪስት እና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የሚመራው የባልደራስ ጉባኤ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ አራት ያቀደውን የሕዝብ ስብሰባ መሰረዝ ነበረበት፡፡ ፓሊስ የተሳታፊዎቹን ደህንነት ለማረጋገጥ አልገኘም በማለቱ ምክንያት መጋቢት 15 ጉባኤው ያቀደውን ስብሰባ የሰረዘ ሲሆን ጉባኤው ለፓሊስ ከሳምንታት በፊት በቅድሚያ አሳውቆ ነበር፡፡ ከአንድ ሳምንት በኋላ ፓሊስ የእስክንድር ደህንነት ያሳስበኛል ሲል ሌላ ስብሰባ እንዳይካሄድ አደረገ፡፡ የጠቅላይ ሚኒሥትር አብይ አፈ ቀላጤ እንደገለጸችው ስብሰባውን ጠቅላይ ሚኒሥትሩ ቢሮ ማድረግ ይችላል ብላ ነበር። በሰኔ ወር ሁለት ጊዜ ፓሊስ የታቀዱ የእስክንድርን የፕሬስ ገለጻዎች ከልክሏል፤ ይሄውም የፕሬስ ገለጻው ሊካሄድበት የነበረው ሆቴል ባለቤት የፕሬስ ገለጻው ለምን እንደሆነ አላወቅኩም ብሎ ለፓሊስ ሪፓርት ካደረገ በኋላ ነበር። ጥቅምት 2 አገሪቱ ከዲሞክራሲ እያሸገሸገች ነው በሚል አቅዶት የነበረውን የሰልፍ ጥሪ እስክንድር መሰረዝ ነበረበት፤ የተሰረዘበትም ምክንያት ጥቅምት 1 የአዲስ አበባ ፓሊስ ስብስቡን በመከልከል መግለጫ ስለ አወጣ ነው። በተጨማሪም የሰልፉን አስተባባሪዎች ፓሊስ ለጊዜው ይዞ ነበር። እስክንድር ለአገር ውስጥ ሚዲያ ከሁለት ሳምንታት አስቀደሞ ስለታቀደው ሰልፍ ለከተማው አስተዳደር እንዳሳወቀ ነግሯል።

### የመደራጀት ነጻነት

ህጉ የመደራጀት ነጻነትና ባልተገደበ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የመሰማራት መብትን ይፈቅዳል፤ ከ2002 ጀምሮ ይሰራ የነበረው ቁጥጥሩ ጥብቅ የሆነውን ሕግ በመተካት በመጋቢት አዲስ የበጎ ፈቃደኛ እና የማህበራዊ አዋጅ፤ እንዲሁም የሲቪል ማህበራዊ ድርጅቶች በመባል የሚታውቅ ሕግ ጸድቋል፤ ይህ አዲስ የሲቪል ማህበራዊ ድርጅቶች ሕግ እርዳታ የመጠየቅ፤ የመቀበል እና ከማንኛቸውም ሕጋዊ በሆኑ ንግዶች እና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴውች ውስጥ ገንዘብ ለማሰባሰብ እና ተልኮውን ለመወጣት ሲል መሳተፍን ይፈቅዳል። አዲሱ ሕግ ቀደም ሲል የነበሩትን ገደቦች ያስወግዳል በይበልጥ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ ለሚደረጉ የፓሊሲ ተሚጋችነት፡፡

### ሐ. የሐይማኖት ነፃነት

በ https://www.state.gov/religiousfreedomreport/ ላይ *የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ሐይማኖቶች ነጻነትን ሪፖርት* ይመልከቱ፡፡

### መ. የዝውውር ነፃነት

ህጉ ለሀገር ውስጥ ዝውውር፣ ለውጭ ሐገር ጉዞ፣ ለመፈለስ፣ እና ከውጭ ለመመለስ የመቻልን ነፃነት ይደነግጋል፡፡ መንግስት በሐገር ውስጥ ለተፈናቀሉ ግለሰቦች፣ ለስደተኞች፣ ከስደት ለሚመለሱ ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ለዜግነት አልባ ሰዎች እና አሳሳቢ ችግር ላለባቸው ሌሎች ግለሰቦች ከለላ እና እርዳታ በመስጠት ረገድ ከተመድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር መ/ቤት እና ከሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ትብብር አድርጓል፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንደ ሐገሪቱ ጠረፎች በመሳሰሉ ለደህንነት ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የመንቀሳቀስ ችሎታቸው በባለስልጣናት ወይም በታጠቁ ቡድኖች ተገድቧል።

<u>የሐገር ውስጥ እንቅስቃሴ/ዝውውር፡-</u> የአገር ውስጥ ሚዲያዎች እንደሚዘግቡት በአማራ/ትግራይ ክልሎች ውስጥ ዓመቱን በሙሉ ሲቪሎች የሚቆጣጠሯቸው የተለያዩ መንገዶች ተዘግተው የቆዩ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ እስከ መስከረም ድረስ ዝግ ነበሩ። መንገዶቹ የተዘጉት በመንግሥት ድጋፍ ባይሆንም የክልሉም ሆነ የፌዴራል ባለሥልጣናት መንገዶቹን ለነፃ እንቅስቃሴ ማስከፈት አልቻሉም፡፡

<u>የውጪ አገር ጉዞ፡-</u> ከጥቅምት 2011 ጀምሮ መንግሥት አቅቦ የነበረውን ወደ ገልፍ አገራት (ሳውዲ አረቢያ እና ኳታር) ጉዞ አንስቷል፤ ማለትም ከሁለቱ አገራት ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት መፈረሙን ተከትሎ በ2006 የሠራተኛ እና አሠሪ አፈላላጊ ድርጅቶች ዜጎችን በማጭበርበር ወደ ውጪ ወስደው ሕገወጥ እና አሰቃቂ ለሆኑ ሁኔታዎች እንደሚዳርጉዋቸው መንግሥት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እቀባ ጥሎ ነበር፤ የተደረሰው ሥምምነት ተቀባይ አገሮቹ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ደህንነት፤ ክብር እና መብቶች መጠበቃቸውን ያስገድዳል፡ ፡ ስምምነቱ በተጨማሪም የሠራተኛ ኢንሹራንስ እንዲኖር እና ገልፍ አገራት ውስጥ ካሉ የመንግሥት ተወካዮች ድጋፍ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

**በሐገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች**

በአለም አቀፍ ፍልሰት ድርጅት በጽሁፍ በቀረበው ዘገባ መሰረት በነሃሴ ውስጥ፤ በግጭት ምክንያት በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ 1,645,867 ግለሰቦች አሉ፤ አብዛኛዎቹም በሶማሌ እና ኦሮሚያ ክልል ውስጥ ነው የሚገኙት። በ2011 በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ቁጥር ኦፊሳላዊ ባልሆኑ ሪፓርቶች 3.2 ሚሊዮን ደርሶ ነበር፤በአለም አቀፍ ፍልሰት ድርጅት በቅርብ በተደረገው የተፈናቀሉ ሰዎች ቆጠራ መሰረት፤ ከዚህ ቁጥር ከግማሽ በላይ ያህሉ የተፈናቀሉት በ2011 ነበር፤ ይህም እስከ ሰኔ ድረስ መሆኑ ነው። ቆጣሪዎቹ የተፈናቀሉትን በትክክል ለመቁጠር በሁሉም የጌዴኦ/ጉጂ እና የወለጋ አካባቢዎች መድረስ አልቻሉም። አብዛኛዎቹ መፈናቅሎች የተከሰቱት በክልሎች መሃከል ነበር። እንዲሁም በጎሳ እና በንብረት ውዝግብ ምክንያት ችግሮቹ የሚከሰቱ ሲሆን የአስተዳደር መጓደል እንዲባባሱ አድርጓቸዋል። በድርቅ፤ በድንገተኛ ደራሽ ውሃ እና በመሬት መንሸራተት ሳቢያ የተፈናቀሉትን ቁጥር የአለም አቀፍ ፍልሰት ድርጅት 518,334 ናቸው ሲል በብዛት የደረሱት በኦሮሚያ፤በሶማሊያ እና በአፋር ክልሎች ውስጥ ነው ። ሌሎች ሁኔታዎች እንደ ልማት ዕቅዶች፤ ማህበራዊ ውጥረቶች እና ተፈጥሮዊ አጋጣሚዎች 71,089 ሰዎች እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆነዋል፡፡

በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች አንድ ወጥ ወይም የማያቋርጥ እርዳታ፤ ካሳ ወይም የመኖሪያ ድጋፍ አያገኙም። መረጃ ሰነዶች ስለሚጎድሏቸው መሰረታዊ የሆኑ እንደ የጤና እንክብካቤ ወይም ትምህርት ወይም በማህበራዊም ሆነ በፓለቲካ እንቅስቃሴዎች የመሳተፍ ዕድላቸው የተወሰነ ነው። ደህንነታቸው ዘላቂነት ይኑረው አይኑረው ሳያረጋግጥ ነው አንዳንድ ጊዜ መንግሥት በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ወደ መጡበት እንዲመለሱ የሚገፋፋው፤ይህም ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ዙር መፈናቀል ያዳርጋቸዋል። ሪፓርቶች እንደሚያሳዩት መንግሥት እንዲመለሱ ለማስገደድ ምግብን እንደ ማባቢያ መሳሪያ አድርጎ ይጠቀማል፡፡

በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በገደብ እና በጌዴኦ ዞን 80,000 የሚደርሱ በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ለሶስት አራት ወራት ያህል መንግስት መዳረሻን በመገደቡ እርዳታ ማግኘት አልቻሉም ነበር። የገደብ ማህበረሰብ አባላት ወደመጡበት አገር እንዲመለሱ አውቶብስ አንሳፈርም ባሉ ጊዜ፤ መንግሥት ቁጥራቸው ከፍ ያለ የጦር ኃይል አሰማርቶ መሳፈራቸው እና የሰፈሩበትም ቦት መነቃቀሉን አረጋግጧል። በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች አውቶብስ እንዳይሳፈሩ ከሚጎትጉቱ ሰዎች ለመከላከል ስል ነው ጦር ያሰማራሁት ይላል መንግሥት። በምስራቅ እና በምዕራብ ወለጋ በትውልድ ቦታዎቻቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ወደ ቤታቸው መመለስ የማይፈልጉበት ዋንኛ ምክንያት ደህንነታቸው ስለሚያሰጋቸው መሆኑን ገልጸዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች፤ በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ቢያንስ ከግንቦት ወር አንድ ወር ቀደም ሲል ወደ ቀድሞ ቦታቸው እንዲመለሱ መንግሥት እርዳት በማቋረጥ እና ሰፈራቸውን በማፍረስ ለመገፋፋት ሞክሯል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሪፓርት እንዳደረጉት በሙቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ በአገራቸው ውስጥ ለተፈናቀሉ ሰዎች እርዳት የማድረግ ችሎታቸውን መንግሥት አግዶባቸዋል።በአገራቸው ውስጥ በተፈናቀሉ ሰዎች ላይ አስከፊ እና ከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረትም አስከትሏል።መንግሥትም ለአንድ ዙር እርዳት ካገኙ በሃላ ብቻ ነው ያነሳቸው። ሕይወት ለማዳን እየተደረገ

ያለውን ሕክምና በማደናቀፍ መንግሥት ያነሳቸው በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ሁሉም ባይሆኑ የመመለስ እርምጃዎች ደህንነታቸውን የጠበቁ፤ በፈቃድ የሆኑ፤ ወይም ክብርን የማይነኩ ናቸው ማለት አይቻልም ይላሉ ሰብዓዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡፡

በምዕራብ ወለጋ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተባባሪ ድርጅቶች እና ባለሥልጣኖች በነሃሴ ወር ባደረጉት ሪፓርት በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ወደ ካማሺ ዞን ሲመለሱ የተወሰዱት በአገራቸው ውስጥ ወደ ተፈናቀሉ ሰዎች ሰፈራ ቦታ ነው። እናም የደህንነት እጥረት መኖሩን፤ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ለመመለስ የተዘጋጁ አለመሆኑን እንዲሁም የመጠለያ እና የመሰረታዊ ግልጋሎቶች ውስንነት መከሰቱን ይገልጻሉ። እነዚህን በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች እንዲረዱ "መጓተት" ይፈጥራል በሚል ሰበብ ለአጋሮች መንግሥት ፈቃድ አልሰጥም ብሏል፤ በተጨማሪም መንግሥት እነዚህ ግለሰቦች በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ናቸው ለማለትም ፈቃደኛ እንዳልሆነ ነው የገለጸው። ይህም ሰብዓዊ የሆነ እርዳታ የመድረስ ዕድሉን ያስወግድዋል። ወለጋ ውስጥ ምግብ የማቅረቡን ሃላፊነት የወሰደው መንግሥት ሲሆን መጀመሪያው ላይ ወጥነት የሌለው እና አናሳ አቅርቦት ነበረው። ይህም ከጊዜ በሃላ ተቋርጦል፡፡

በሐምሌ ወር መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የከለላ አጋሮች ባደረጉት ቅኝት ወደ ትውልድ አገራቸው ላልተመለሱ ሰዎች መንግሥት ሰብአዊ እርዳታ ማቋረጥ መቀጠሉን በድጋሚ አረጋግጠዋል። በጌዴኦ እና ምዕራብ ጉጂ በመንግሥት አነሳሺነት የጋራ እርምጃዎች በሚካሄዱበት ጊዜ በነበሩ ሁኔታዎች ላይ በመመረኮዝ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ግለሰቦች ለመለየት ጥረት ሲደረግ በአገራቸው ውስጥ ተፈናቅለው ቦታ ሳያገኙ የቆዩ ሰዎች በዚህ ግምገማ ወቅት አልተመዘገቡም፤ ይህም የሆነው ለመተግበር አቅም በማጣት እና መድረስ ባለመቻሉ ነው። ጌዴኦ ያለውም አስተዳደር እነዚህ በአገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመለየት በተደረገው እንቅስቃሴ ከቆጠራ እንዳገለለ አምኗል፤ ለተፈናቀሉት ሰዎች እርዳታ እንዲቀርብም ሁኔታ አላመቻቸም፡፡

**የስደተኞች ጥበቃ**

ሐገሪቱ ከሐምሌ ወር ጀምሮ 655,105 ስደተኞችን አስተናግዳለች፡፡ ብዙ ስደተኞች የመጡባቸው ሐገራት ደቡብ ሱዳን (303,733) ፣ ሶማሊያ (175,961)፣ ኤርትራ (100,566)፣ ሱዳን (50,777) ነበሩ፡፡

<u>ጥገኝነት የማግኘት እድል፡-</u> ህጉ የጥገኝነት ወይም የስደተኝነት ደረጃ ለመስጠት የደነገገ ሲሆን፣ መንግስት ለስደተኞች አገልግሎት እና ጥበቃ ለመስጠት በስደተኝነት ደረጃ መወሰኛ ስርዓት ተጠቅሟል፡፡

<u>የሥራ ቅጥር፡-</u> በአገር ውስጥ ያሉ ስደተኞችን መብት በሰፊው ለማጎልበት ጥር 9 ፓርላማው አዲስ ሕግ አጽድቋል። የስደተኛ ሕጉም ለስደተኛ ሥራ የመሥራት ፈቃድ እንዲሁም መሰረታዊ ትምህርት እና የፋይናንስ ዕድል እንዲያገኝ፣ የመንጃ ፈቃድ እንዲያወጣ፣ ልደት ፣ ጋብቻእና ሞት እንዲያስመዘግብ ያስችለዋል። የሥራ ፈቃዱ እንዴት ሥራ ላይ እንደሚውል እና ማን ብቁ እንደሆነ ግን ሕጉ ግልጽ አላደረገም፡፡

<u>ዘላቂ መፍትሔዎች፡-</u> መንግስት ስደተኞችን በሐገሪቱ ውስጥ እንዲኖሩ ያስተናገደ ቢሆንም ዜግነት ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ አልገለጸም ወይም ውህደት እንዲፈጽሙ አላደረገም። ኢትዮጵያዊ ዜጋ ድጋፍ ካደረገላቸው ከኤርትራ የመጡ ስደተኞች ከሰፈራ ጣቢያ ውጪ ወጥተው ለመኖር ብቁ ናቸው፤ ይህም ኤርትራዊያን ስደተኞችን ከሌላው ስደተኛ የተለዩ ያደርጋቸዋል። ፈተናዎችን ያለፉ ስደተኛ ተማሪዎች በመንግስትና በዩኤንኤችሲአር (ስደተኞች ጉዳይ ድርጅት) ክፍያ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን መከታተል ችለዋል። ከአለም አቀፍ የስደተኞች ማህበር እኩል ለመጓዝ ሲባል በባምባሲ የስደተኞች ጣቢያ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ውስጥ ስደተኞች ልደት፤ ጋብቻ፤ ፍቺ፤ እና ሞት ማስመዝገብ ይችሉ ዘንድ በሰኔ ወር ዩኤንኤችሲአር፤

ዩኒሲኤፍ፤ የኢትዮጵያ ጠቃሚ መረጃዎች ምዝገባ ድርጅት እና የስደተኞች እና ተመላሾች ጉዳይ መስሪያ ቤት መመዝገቢያ ማዕከል ከፍተዋል፡፡

በአገሩ ውስጥ 3ኛ ደረጃ ያለው የምዝገባ እንቅስቃሴ ዩኤንኤችሲአር እና የስደተኞች እና ተመላሾች ጉዳይ መስሪያ ቤት በሃምሌ ወር ውስጥ አጠናቀዋል። በዚህ መዝገብ ውስጥ ያለው የተመዘገቡ የስደተኞች ቁጥር ከ 905,831 ወደ 655,105 ቀንሷል። ምዝገባ በአዲስ አበባ እና በሁሉም 26ቱ የስደተኞች ጣቢያዎች ውስጥ ይካሄዳል። የተመዘገቡ ስደተኞች ቁጥር ያነሰበት ምክንያቶች፤ የዘላን ባህሪ ስለአላቸው እንዲሁም በምዝገባ ወቅት ስላልተገኙ፣ በድጋሚ የተመዘገቡ ስለነበሩ፣ ዜጎች በተፈናቀሉ ጊዜ ስደተኞች ነን ብለው የተመዘገቡ ስለተገኙ እና ጥቂቶች ሳይታሰብ ወደ ደቡብ ሱዳን በመመለሳቸው ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ሠ፤ ዜግነት የሌላቸው ግለሰቦች

ተፈጻሚ አይደለም

**ክፍል 3፡ በፖለቲካ ሂደት የመሳተፍ ነፃነት**

ዜጎች በምስጢር የድምጽ መስጫ እንዲሁም በአለምአቀፍና በተስተካከለ ምርጫ መሰረት በሚካሄዱ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫዎች መንግስታቸውን ለመመረጥ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ የገዢው ፓርቲ የምርጫ እድሎች ግን ይህንን ሁኔታ ገድበዋል፡፡

***ምርጫዎችና ፖለቲካዊ ተሳትፎ***

*<u>የቅርብ ጊዜ ምርጫዎች፡-</u>*ሐገሪቱ በ2007 ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብሔራዊ ምርጫዎች አካሄዳለች፡፡ በዚያው ዓመት ዘግየት ብሎ ፓርላማው ጠቅላይ ሚኒስትር በማድረግ ኃ/ማርያም ደሳለኝን በባለሙሉ ሃላፊነት መርጧል፡፡ በካቲት 2010 ኃ/ማርያም ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን በፈቃዳቸው መልቀቃቸውን ያስታወቁ ሲሆን፣ በመጋቢት 2010 ኢሕአዴግ አብይ አህመድን የፓርቲው አዲስ ሊቀመንበር እና ለፌዴራል ጠቅላይ ሚኒስትርነት እጩ አድርጎ መርጧቸዋል፡፡ ከዚያም በተወካዮች ም/ቤት የድጋፍ ድምፅ ከተሰጠ በኋላ አብይ አህመድ መጋቢት 24 የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ስልጣን ይዘዋል፡፡

በ2007 የብሔራዊ ፓርላማ ምርጫዎች ኢሕአዴግ እና አጋር ፓርቲዎች ለአምስተኛ ጊዜ ተከታታይ የአምስት ዓመት የሥልጣን ዘመን ለፓርቲው ሲሰጡ ሁሉንም 547 መቀመጫዎች አሸንፈው ነበር፡፡ የመንግስት ክልከላዎች የድምጽ አሰጣጡን ገለልተኛ ታዛቢነት አጥብቀው ገድበዋል፡፡ ምርጫዎቹን ለመታዘብ በብቸኝነት የተፈቀደለት አለምአቀፍ ድርጅት የአፍሪካ ሕብረት ብቻ ነበር፡፡ የሐገር ውስጥ ፖሊሶች ጣልቃ በመግባት፣ በመተናኮል እና ከፍ/ቤት ትዕዛዝ ውጭ በማሰር በተቃዋሚ ፓርቲ ታዛቢዎች ተከሰዋል፡፡ ከምርጫዎቹ በፊት ስድስት ዙር የሚዲያ ክርክሮች የተደረጉ ሲሆን፣ የውስጥ ሚዲያ ባጠቃላይ ክርክሮቹን በሙሉ ሲያስተላልፍ በጥቂቱ ብቻ ዓርትኦ ተደርገዋል፡፡ ክርክሮቹ ለምርጫው የሚወዳደሩ ትላልቅ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሁሉ አካተዋል፡፡

ገለልተኛ ጋዜጠኞች ምርጫውን ሲዘግቡ መጠነኛ ችግር እንዳጋጠማቸው ገልጸዋል፡፡ አንዳንድ ገለልተኛ ጋዜጠኞች ተገቢና ወቅታዊ ማመልከቻዎችን በወቅቱ ካቀረቡ በኋላ ከምርጫው አንድ ቀን በፊት ነበር የታዛቢነት ሹመት እንደተቀበሉ ሪፖርት ያደረጉት፡፡ ከ1997 አወዛጋቢው የብሔራዊ ምርጫ አንስቶ የተተገበሩ በርካታ ህጎች፣ ደንቦችና የአሰራር ስርዓቶች በምርጫው ሂደት ሁሉ ለኢሕአዴግ በግልጽ ያዘነበለ እድል ፈጥረዋል፡፡ ተቃዋሚ እጩዎችንና ደጋፊዎችን ማስፈራራትን ጨምሮ የተዛቡ የመንግስት ዘዴዎች ሪፖርት ተደርገዋል፡፡ ከምርጫዎቹ በፊትና ወዲያው ይህንኑ ተከትሎ ባለው ወቅት ቢያንስ ስድስት ከምርጫ

ጋር የተያያዙ የሞት አደጋዎች መከሰታቸውን የተለያዩ ሪፖርቶች ገልፀዋል፡፡ ለመራጮች ትምህርት ለመስጠት ብቸኛ ሃላፊነት ያለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ሲሆን፣ ለመራጮች ስለሚሰጥ ትምህርት በብዙ የሐገር ውስጥ ቋንቋዎች የሬዲዮ ፕሮግራሞችን እና የመምሪያ መፅሐፎችን አሰራጭቷል፡፡

በቅድመ ምርጫ የዳሰሳ ጥናት የአፍሪካ ሕብረት የ2007ቱን ምርጫዎች "የተረጋጉ፣ ሰላማዊና ተዓማኒነት ያላቸው" ሲል በመጥራት መንግስት ላደረጋቸው የምዝገባ ጥረቶች አድናቆቱን ገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ምርጫው ያጠነጠነበትን ህጋዊ ማዕቀፍ አስመልክቶ አሳሳቢ ያላቸውን ነጥቦች አንስቷል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ከ35 ሚሊዮን በላይ መራጮችን የመዘገበ ሲሆን ማናቸውንም ፍትሐዊ ያልሆኑ የድምጽ ሰጪዎችን የምዝገባ ድርጊቶች አልዘገበም፡፡

ፓርላማ የአካባቢ ምርጫዎችን ከግንቦቱ ብሄራዊ ምርጫ ጋር አጣምሮ በነሃሴ ወር እንዲካሄዱ ወስኗል፡፡ የፌዴራሉን እና የአካባቢን ምርጫ በአንድ ላይ ለማካሄድ ፓርላማ ያቀረበውን ሃሳብ ብሄራዊ የኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ ገና በይፋ አልተቀበለም፡፡

<u>የፖለቲካ ፓርቲዎችና ፖለቲካዊ ተሳትፎ:-</u> በኢሕአዲግ ቁጥጥር ስር ያለው መንግስት በትጥቅ ትግል ላይ ያሉትን ጨምሮ ተቀማጭነታቸው በውጭ ሐገር የሆኑ ተቃዋሚ ቡድኖች ተመልሰው ከነውጥ የጸዳ ትግል እንዲያካሂዱ በ2010 ጥሪ አቀረበ፡፡ በተግባራዊ ሁኔታ ኦነግን፣ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባርን፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባርን እና አግ7ን ጨምሮ ሁሉም ትልልቅ ተቃዋሚ ቡድኖች ጥያቄውን ተቀብለው ወደ ሐገሪቱ ተመለሱ፡፡ የተመለሱት ፓርቲዎች እና አዲስ የተመሰረቱት ፓርቲዎች አገር ውስጥ መንቀሳቀስ ቀጥለዋል፡፡ አንዳንድ ፓርቲዎች፤ ኦነግ፣ የአማራ ፓለቲካ ንቅናቄ፣ የትግራይ ብሄራዊ አላያንስ ለዲሞክራሲ የመሳሰሉትን ጨምሮ መረጋጋት ባለመኖሩ እንዲሁም ማስፈራራት እና አባሎቻችን ላይ ጥቃት ደረሰብን በማለት በአገር ውስጥ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ቢሮ ለመክፈትም ሆነ ለመንቀሳቀስ አልቻልንም ይላሉ።

ገዢ ፓርቲውን ከብሄር ፓለቲካ ለማላቀቅ እና የኢኮኖሚ እድገት ለማስጨበጥ በታህሳስ ወር ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ኢሕደግን ፈረካክሰው የብልጽግና ፓርቲን መስርተዋል፡፡ የቀድሞው የኢሕደግ ቅንጅት አባል የነበረው ይትግራይ ሕዝቦች ነፃ አውጪ ድርጅት አዲሱ ፓርቲ ውስጥ መደመርን አሻፈረኝ ብሎአል።

የትግራይ አላያንስ ለብሄራዊ ዲሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር አረጋዊ በርሄ ሰኔ 19 መቀሌ ውስጥ ለቀብር በተገኘ ጊዜ በትግራይ ክልል ፓሊስ ተይዞ የግድያ ሙከራ ተደረገበት ሲል ፓርቲው ሪፓርት አድርጓል፡፡ የወጣት ቡድኖች ሊያጠቁኝ ሞክረው ነበር ብሏል አረጋዊ፡፡ ይህንንም ተከትሎ ፓሊስ ወደ ኩሂያ እስር ቤት ወስዶኝ ሌሊቱን ሙሉ ያለምንም ማብራሪያ በቁጥጥር ስር አቆይቶኛልም ብሏል፡፡ ዘግይቶ ሌላኛው የትግራይ አላያንስ ለብሄራዊ ዲሞክራሲ ፓርቲ አባልን አማኑኤል ሊባኖስን አራት ፓሊሶች ወደ ጫካ በመውሰድ በግድ መረዙት። አማኑኤል ግን ከጥቃቱ ተርፏል።

የኢሕአዲግ አባል ፓርቲዎች ለአባላቶቻቸው ጥቅማ ጥቅሞችን በማከናነብ ፓርቲው ብዙ የንግድ ድርጅቶችን በቀጥታ በባለቤትነት በመያዝ ለታማኝ ደጋፊዎቹ ስራዎችና የንግድ ስራ እድሎችን ከፈተ፡፡

የተመዘገቡ የፖለቲከ ፓርቲዎች የሐገር ውስጥ ቢሮዎችን በየአካባቢው ለመክፈትና ለመከራየት ከክልል መንግስታት ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ከ2020 ብሔራዊ ምርጫ አስቀድሞ በዓመቱ ውስጥ ብዙ ቢሮዎች ለመክፈት መቻሉን ቢያንስ አንድ ትልቅ ተቃዋሚ ፓርቲ ሪፖርት አድርጓል፡፡ "ህዝባዊ ስብሰባዎችን" ሪፖርት እንዲያደርጉና ለህዝብ የድጋፍ ሰልፎች ፈቃድ እንዲያገኙ የሚያስገድዱ ህጎች የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ገድበዋል፡፡ በኦሮሞ እና በአማራ ክልል ውስጥ ቢሮ እና የሰብሰባ አዳራሾች ያለእንቅፋት መከራየት ችለናል ይላሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች፡፡ ቢሆንም ግን፤ በደህንነት ችግር እና የአካባቢ የመንግሥት ባለሥልጣናት እንቅፋት በመሆናቸው ምክንያት ኦሮሚያ ውስጥ ባሉ አንዳንድ ቦታዎች የኢትዮጵያ ዜንች

ለማህበራዊ ፍትህ ቢሮ መክፈት አልቻልኩም ይላል፡፡ ከገዢው ቅንጅት ድርጅት ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሥራ አጥ ወጣቶች ሥራ ለማግኘት "የድጋፍ ደብዳቤ" ከወረዳቸው ማግኘት እንዳልቻሉ ሪፓርቶች ያሳያሉ።

የሴቶችና የአናሳ ቡድኖች ተሳትፎ፡-በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ ሴቶች በፖለቲካ ሕይወት እንዳይሳተፉ የሚገድቡ የአባታዊ ስርዓቶች ቢኖሩም ሴቶች ወይም አናሳ ቡድኖች ድምጽ ከመስጠት ወይም በፖለቲካ ሕይወት ከመሳተፍ የሚያግዳቸው ህግ የለም፡፡ መሻሻሎች ቢኖሩም ግን ሴቶች ለስራ መደቦች በመመረጥ እና በመሾም በጉልህ ሁኔታ ውክልናቸው አንሶ ቆይቷል፡፡ በጥቅምት 2011 ጠቅላይ ሚኒስትሩ 10 የሴት ሚኒስትሮች ያሉበትን አዲስ ካቢኔ አዋቅረዋል ወይም በተያዘው ካቢኔ ግማሽ እንደሆኑ አሳውቀዋል፡፡ በተጨማሪም በጥቅምት 2011 ሳህለወርቅ ዘውዴ የሐገሪቱ የመጀመሪያ የሴት ፕሬዘዳንት ሆነዋል፡፡ የሳህለወርቅ ዘውዴ ሹመት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአስተዳደራቸው ውስጥ የሴቶችን አቅም ለማጎልበት ከገለፁት ግብ ጋር የተጣጣመ ነበር፡፡ በሕዳር ወር ፓርላማው የሐገሪቱን የመጀመሪያ ሴት የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዘዳንት ቃለ መሐላ አስፈፀመ፡፡ በብሔራዊ ፓርላማ ውስጥ ሴቶች 39 በመቶ መቀመጫዎች፣ ማለትም ከ547 ውስጥ 211 ይዘዋል፡፡

የመንግስት የብሔር ፌዴራሊዝም ፖሊሲ በፌዴሬሽን ም/ቤት (በላይኛው የፓርላማ ምክር ቤት) ለሁሉም ትልልቅ የብሔር ቡድኖች ውክልና ለመስጠት የተናጠል መራጭ ማህበረሰብ ምስረታን አስከትሏል። መንግስት ከ80 በላይ ለሆኑ ብሔረሰቦች እውቅና የሚሰጥ ሲሆን፣ ቢያንስ አንድ አባል በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውስጥ እያንዳንዱን "ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ እና ህዝብ" እንደሚወክል ህገ መንግስቱ ይገልጻል፡፡

## ክፍል 4፡ በመንግስት ውስጥ ሙስና እና የግልጽነት እጦት

ህጉ ለሙስና ጥፋት የወንጀል ቅጣቶችን ይደነግጋል፡፡ መንግስት ህጉን በተሳካና በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አላደረገም፡፡

ሙስና፡- ሙስና በተለይም ጉቦ መጋበዝ ፖሊሶችንና የፍትሕ ሙስናን ጨምሮ በአዋኪነት ዘልቋል፡፡ የመንግስት ባለስልጣናት የመሬት ምደባ ሂደቱን እንደጠመዘዙና በመንግስት ወይም በፓርቲ ባለቤትነት ስር ያሉ የንግድ ድርጅቶች በግንባር ቦታ ላይ ለሚገኙ የመሬት ሊዞች እና ብድር አድሎአዊ እድል ማግኘታቸውን አንዳንድ ባለድርሻ አካላት ያምናሉ፡፡ ጠቅላይ አቃቤ ህግ የሙስና ክሶችን እንዲመረምርና ክስ እንዲመሰርት ህጉ ሃላፊነት ሰጥቶታል፡፡

በጥር ወር 2010፣ በዘዴ የተፈፀሙ የሙስና ክሶችን የመመርመር ስልጣን ያለው የሙስና ዳይሬክቶሬት በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ መቋቋሙን የቀድሞው ጠ/ሚ ኃ/ማሪያም አውጀዋል፡፡ መንግስት የምርመራ ቢሮውን የመሰረተበት ምክንያት በመንግስት ቢሮክራሲ ውስጥ ሁሉ ግልጽነትን ለማጎልበት ነው። ጥር 15 የጥረት ኢንዳውመንት የቦርድ ሊቀመንበር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሙስና እና የአስተዳደር ማጉደል ወንጀሎችን ፈጽመሃል በማለት የአማራ ክልል ፓሊስ በፌዴራል ፓሊስ በመታገዝ በረከት ሲሞዖንን ወንጅሎ በቁጥጥር ስር አደረገ፡፡ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሠረት የቀድሞውን የብሄራዊ ጥበቃ እና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር የነበረውን ጌታቸው አሰፋን ሚያዝያ 29 የፌዴራል አቃቢ ሕግ ወንጅሎታል።

ሐብትን ስለማሳወቅ፡- ሁሉም የመንግስት ባለስልጣናትና ሰራተኞች ሐብታቸውንና የግል ንብረታቸውን እንዲያስመዘግቡ ህጉ ያስገድዳል፡፡ ህጉ ደንብን በማያካብሩ ላይ የገንዘብና የወንጀል ቅጣትን ያካትታል፡፡ የፌዴራል የስነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን የፋይናንስ ማሳወቂያ ሪከርዶችን ይይዛል፡፡ በህጉ መሰረት እነዚህን ሪከርዶች ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የጽሑፍ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፤ የማሳወቅ ድርጊት አስፈላጊነቱ በኮሚሽኑ ካልታመነበት በስተቀር የቤተሰብ ሐብት መረጃዎችን ማግኘት ሊገደብ ይችላል፡፡

**ክፍል 5፡ ተፈፀሙ በተባሉ የሰብዓዊ መብቶች ላይ አለምአቀፋዊና መንግስታዊ ያልሆነ ምርመራን በተመለከተ መንግስት ያለው አመለካከት**

ጥር 28 ከፍ ባለ መልኩ የተከለሰ እና የተጠናከረ ሲኤስፒን (አዋጅ ቁ 1113/2019) በተለምዶ ሲኤስኦ በመባል የሚታወቀውን ሕግ ፓርላማው አጽድቋል፡፡ ተሚጋች የሲቪል ድርጅቶች ከዚህ ቀደም ገንዘብ ከውጪ አገራት መንግሥታት እና ከግል ዘርፉ እንዳያገኙ በከፍተኛ ሁኔታ ይከለክላቸው የነበረውን ገደብ አንስቶላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሕጉ የውጪ አገር በጎ ፈቃደኞች ሲኤስኦ ውስጥ እስከ አንድ አመት ድረስ እንዲሰሩ ይፈቅዳል፡፡

በዚህ ዓመት ውስጥ የተሳተፉት የአገር ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ቁጥራቸው ትንሽ ነው፡፡ ምርመራ የማካሄድ አቅም ያለው እና ነፃ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ቡድን አገር ውስጥ ያለ ቢኖር ብቸኛው እና የሃብት ፈተና ያለበት ሰመኮ (ኤችአርሲኦ) ነው፡፡ በአባላቱ የሚደገፍ፤ ወገንተኛ ያልሆነ፤ መንግሥታዊ ያልሆነ፤ እና ለትርፍ ያልቆመ ብቸኛ አካል ነው፡፡ በ1983 ከተመሰረተ ወዲህ ከ 100 በላይ ሪፓርቶችን አቅርቧል፡፡ በዚህ ዓመት ያቀረበው ሪፓርት የሚያሳየው በብሄር ተነሳሽነትን የደረሱ ጥቃቶችን፤ ግጭቶችን እና መፈናቀሎችን ነው፡፡

በአጠቃላይ መንግስት በሐገር ውስጥ እንዲሁም በዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቡድኖችና ታዛቢዎች ላይ እምነት ማጣትና የተሰላቸ ቢሆንም ያ አመለካከትና እምነት ማጣቱ እየተለወጠ መሄዱ ይታያል፡፡ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ ሚዲያዎች እንደ ሂውማን ራይትስ ዎች የመሳሰሉ ዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብት ቡድኖችን ይተቻሉ፡፡ በነሃሴ 2010 ውስጥ አራት የሐገር ውስጥ የበጎ አድራጎቶች እና የመብት ድርጅቶች፣ ለሰብዓዊ መብት ቡድኖች ጥብቅና በመቆም እና የመብት ተቆርቋሪ ቡድኖች እንዲንቀሳቀሱ ሰፊ ምህዳር በመስጠት ላይ ያተኮረ የኢትዮጵያ መብቶች ድርጅቶች ኮንሶርቲየም የሚባል አዲስ የመብቶች ቡድን ጀመሩ፡፡

አዲስ በወጣው ሲኤስኦ ሕግ ሥር በመመዝገብ በሃምሌ ወር ውስጥ ቀደም ሲል በውጪ አገር ይገኝ የነበረው የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ሊግ አገር ውስጥ መንቀሳቀስ ጀመረ። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ ፕሮጀክት፤ ከባህር ማዶ ይገኝ የነበር ቡድን በሃምሌ ወደ አገር በመመለስ ዜጎች በዲሞክራሲ እና ሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ መብቶቻቸውን ያውቁ ዘንድ፤ ከትትል ለማድረግ እና ተሚጎች ለመሆን በመብቶች እና ዲሞክራሲ ማስፋፊያ ማዕከል ስም ተመዘገበ። ጠበቆች ለሰብዓዊ መብቶች የሚል የአገር ውስጥ ቡድንም በጥር ወር ውስጥ የፌዴራል የበጎ አድራጎት እና ማህበራት ኤጀንሲ ተመዝግቦ ፈቃድ አወጣ።

አብዛኞቹ መያድ (እንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) ወደ ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎችና ሌሎች የማሰሪያ ቦታዎች እንዳይደርሱ በመንግስት ተከለከሉ። መንግስት ታራሚዎችን እንዲጎበኝ የፈቀደለት ለጀስቲክስ ፎር ኦል-ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ ሲሆን፣ ይህ ድርጅት ከውጭ ምንጮች ያልተገደበ የገንዘብ እርዳታ እንዲሰበስብና ለሰብዓዊ መብቶች ጥብቅና ለመስማራት የሚያስችለው ከግዴታ ነፃ የሆነ መብት ነበረው፡፡ አንዳንድ ሌሎች መያድ የታራሚዎችን ምህረት የማግኘት እድል በማሻሻል ረገድ አዎንታዊ ሚና ተጫውተዋል፡፡

የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፣ ሚዲያ፣ የበጎ አድራጎት ኤጀንሲዎችና የዲፕሎማቲክ ልዑኮች ወደ አንዳንድ አካባቢዎች እንዳይደርሱ በባለስልጣናት ተገደቡ፡፡ መንግስት ወደ አስጊ አካባቢዎችና ክልሎች መያድ መግባት ስለሚያስችላቸው መብት ግልጽ መመሪያ ማጣቱን የቀጠለ ሲሆን፣ የክልል መንግስት ባለስልጣናት እና ወታደራዊ ባለስልጣናት የመያድን የመግቢያ መብት ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ወደ ፌዴራል መንግስት ባለስልጣናት እንዲያስተላልፉ አድርጓል። ጋዜጠኞች ወደ አስጊ ክልሎች ከመግባታቸው በፊት እንዲመዘገቡ ባለሥልጣናት የጠየቁ ሲሆን በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ እንዳይገቡም ከልክለዋል፡፡ ለተወሰነ ወቅት የደህንነት

ስጋቶችን እንደምክንያት በመጥቀስ የክልል ፖሊሶች ወይም የአካባቢው ሚሊሻዎች መያድ ወደ ልዩ አካባቢዎች እንዳይገቡ ስለማገዳቸው ሪፖርቶች ነበሩ።

<u>የመንግስት የሰብዓዊ መብት አካላት:-</u> የእምባ ጠበቂ ቢሮ የማረሚያ ቤት ሁኔታዎችን መመርመር ጨምሮ በዋና የቅርንጫፍ ቢሮዎችና በባለስልጣናት የተፈፀሙ የብልሹ አስተዳደራዊ ተግባራትን ቅሬታዎች የመመርመር ስልጣን አለው፡፡ ከሃምሌ 2010 እስከ ጥር ድረስ ቢሮው 853 አቤቱታዎች ደርሰውኛል ሲል ለፓርላማ አሳውቋል፤ ከእነዚህ ውስጥ 455 ከእርሱ ቢሮ ሃላፊነት ውጪ ናቸው ብሎአል፡፡ ምርመራ ካካሄደባቸው 488 ጉዳዮች ውስጥ 262 የአስተዳደር መጓደል አልተፈጸመባቸውም ብሎ ደምድሟል፡፡ የቀሩት አቤቱታዎች ለስድስት ወራት ያህል እስከ ጥር ድረስ በምርመራ ላይ ነበሩ። የዚህን ቢሮ የሥራ አፈጻጸም ብቁ አይደለም ሲል የፓርላማው የሕግ፤ ፍትህ፤ እና ዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ጉባኤ ሃሳብ ሰጥቷል።

ኢሰመጉ በሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ጥናት አድርጎ በሱማሌ እና በኦሮሚያ በተከሰቱ ግጭቶች እንዲሁም በምዕራብ ጉጂ ዞን ኦሮሚያ ውስጥ እና በጌዴኦ ዞን ደቡብ ክልል ውስጥ ባጋጠሙ ግጭቶች ሳቢያ የደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ ምርመራ አካሂዷል። ጉባኤው እነዚህን ግኝቶቹን ይፋ አላደረገም፡ ፡ በመስከረም 2011 ጅጅጋ የሚገኘው ቅርንጫፍ ቢሮው ከወር በፊት በነሃሴ 2010 የተነሳውን ሁከት ተከትሎ በወጣቶች እና በደህንነት ሃይሎች ጥቃት ከደረሰበት በኋላ መከፈቱን ኢሰመጉ አሳውቋል።

## ክፍል 6፡ መገለል፣ ማህበረሰባዊ የመብት ጥሰት እና ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር

የመንግስት ፖለቲካዊ ለውጥ (ትራንስፎርሜሽን) ከመንግስት ሐይሎች ጋር በሚደረግ ውጊያ የሞት ብዛትን ለመቀነስ አስተዋፅዖ ባደረገበት ሁኔታ፣ በማህበረሰቦችና በዜጎች መሃከል የሁከት መጠን መጨመር ጀምሯል።

### ሴቶች

<u>አስገድዶ መድፈርና የቤት ውስጥ ጥቃት:-</u> ህጉ አስገድዶ መድፈርን ወንጀል በማድረግ በጉዳዩ ከባድነት ላይ በመመስረት ከ5 እስከ 20 ዓመት የእሥር ቅጣት ይደነግጋል፡፡ ህጉ በትዳር ጓደኛ ለሚፈፀም የአስገድዶ መድፈር ጉዳይ በግልጽ አስተያየት አይሰጥም፡፡ በትዳር ጓደኛ የሚፈፀም አስገድዶ መድፈርን በልዩ ሁኔታ ሳይገልጽ በትዳር ጓደኛ ወይም በደንበ-ወጥ ህብረት አብሮ በሚኖር ግለሰብ ላይ የሚፈፀምን ጥቃት በአጠቃላይ ይሸፍናል፡፡ አንዳንድ ዳኞች ይህ አንቀፅ በትዳር ጓደኛ የሚፈፀሙ የአስገድዶ መድፈር ጉዳዮችን እንደሚሸፍን ቢተረጉሙም ሌሎቹ ግን እንዲህ አይነት ጉዳዮችን ችላ ብለው ያልፋሉ። መንግስት ህጉን ሙሉ በሙሉ አላስከበረም።

የቤት ውስጥ ጥቃት በሕግ የተከለከለ ነው፤ ቢሆንም ግን መንግስት ወጥነት ባለው መልኩ አይደለም ሕጉን የሚያስከብረው። በደረሰው ጉዳት አስከፊነት መጠን ላይ ተመስረቶ ቅጣት ከአነስተኛ የገንዘብ ቅጣት አንስቶ እስከ 15 ዓመታት በእስር ሊያስቀጣ ይችላል፡፡ በትዳር ጓደኛ የሚፈጸምን ጥቃት ጨምሮ የቤት ውስጥ ጥቃት የተስፋፋ ማህበራዊ ችግር ነው፡፡ በ2009 የስነ-ህዝብ ስብጥር እና የጤና ቅኝት ጥናት (DHS) መሰረት 34 በመቶ ያገቡ ሴቶችና ከ15 እስከ 49 ዓመት ያሉ ሴቶች በትዳር ጓደኛ የሚፈፀም አካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም ስሜታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡

<u>የሴት ብልት መግረዝ/መቁረጥ (FGM/C):-</u> የሴት ልጅ ግርዛት/የብልት አካል መቁረጥ ህገ ወጥ ሲሆን በወንጀሉ ሁኔታ ላይ በመመስረት እስርንና መቀጫን የሚያካትት ቅጣት አለው፡፡ መንግስት ይህንን ክልከላ በንቃት አላስከበረም፡፡ በ2019 ዲኤችኤስ ያወጣው ሪፓርት እንደሚያሳየው ከመቶ 65 ልጅ አገረዶች እና ሴቶች እድሚያቸው ከ15 እስከ 49 የሆነ የሴት ብልት መግረዝ/መቁረጥ ይፈጸምባቸዋል፡፡ የሴት ብልት

መግረዝ/መቁረጥ የሚፈጸመው በከፍተኛ ደረጃ በሱማሌ ክልል (ከመቶ 99) እና በዝቅተኛ ደረጃ ትግራይ ክልል (ከመቶ 23) ሲሆን፤ በከተማዎች ልምዱ በጣም የቀነሰ ነው፡፡

ቂንጥር የመቁረጥ ልማድ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ በወንጀል የሚያስጠይቅ ሲሆን በጉዳት አድራሾቹ ላይ የሶስት ወራት እስር ወይም ቢያንስ የ500 ብር (17 ዶላር) መቀጫ ይደነግጋል፡፡ የሴት ልጅን የመራቢያ አካላት ቆርጦ መስፋት (በጣም ከባዱና አደገኛው የብልት ግርዘት/የመስፋት ተግባር) ከአምስት እስከ 10 ዓመት በእስር ያስቀጣል፡፡ በመንግስት ምንጮች መሰረት በሴት ልጅ ግርዛት/የመራቢያ አካል መቆራረጥ ላይ የወንጀል ክስ ያልነበረ ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ ህጉ ስለመተግበሩ ሚዲያዎች ሪፖርት አድርገዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃዎች አባሪ “ሐ”ን ይመልከቱ፡፡

ሴሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፡- መንግስት ድርጊቱን ለማስቆም ሙከራዎች እያደረገ ሳለ በአንዳንድ ክልሎች የቀጠለ ቢሆንም በጠለፋ ጋብቻን መፈፀም ህገ ወጥ ነው፡፡ በግዴታ የወሲብ ግንኙነቶችን መፈፀም በአብዛኛው ጋብቻዎች በጠለፋ እንዲደመደሙ የሚያደርግ ሲሆን ሴቶች ዘወትር በጠለፋ ወቅት አካላዊ መጎሳቆል ይደርስባቸዋል፡፡ የጠለፋ ተግባራት በቤተሰቦች፣ በማህበረሰቦች እና በጎሳ ቡድኖች መካከል ግጭቶችን ያስከትላሉ፡፡ አጥፊው ወገን ጠለፋ ፈጽሞ ተበዳይዋ አጥቂውን ለማግባት ከተስማማች ቅጣት አይደርስበትም፡፡

ወሲባዊ ጉትጎታ/ንዝንዝ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በተከሳሽ ላይ ከ18 እስከ 24 ወራት የሚደርስ ቅጣትን የሚያዝዝ ሲሆን ባለስልጣናት ግን በአብዛኛው ህጉን አላስከበሩም። ወሲባዊ ጉትጎታ በብዛት ተሰራጭቷል።

የህዝብ ብዛትን በመቆጣጣር ረገድ የሚኖር ግዳጅ፡- በግዴታ ስለተፈፀመ የጽንስ ማስወረድ ወይም ያለ ውዴታ መካን ስለመደረግ ሪፖርቶች አልነበሩም፡፡

መገለል፡- ሁሉም የፌዴራል እና የክልል ሕጎች ሴቶች የመንግስት መሬት እንዲያገኙ መብት ይሰጣሉ፡፡ የውርስ ሕጎችም ባለቤታቸው ለሞቱባቸው ሴቶች በጋብቻ ጊዜ የፈራን የጋራ ንብረት እንዲወርሱ ይደነግጋሉ፤ ቢሆንም ግን ሁለቱንም ሕጎች መተግበር ላይ ሲመጣ የተዛባ ነው፡፡ ሴቶችን ማግለል የተስፋፋ ነበር፡፡ ከመቶው 80 እጁ የሚኖርባቸው ገጠራማ ስፍራዎች ላይ በብዛት ጎልቶ ታይቷል።

የትምህርት ደረጃቸው አነስተኛ በመሆኑ እና በባህላዊ አመለካከት ምክንያት ሴቶች ሥራ፤ ብድር፤ ወይም ንግድ የመጀመርም ሆነ የማስተዳደር ሁኔታቸው ውስን ነው፡፡ የአራት ወር የወሊድ ፈቃድ ያገኙ ዘንድ በሃምሌ ፓርላማው የሠራተኞች ሕጉን አሻሽሎ አውጥቷል፡፡ ሴቶች እነዚህ ቁጥራቸው ሰፋ ያለን የኢኮኖሚ ሃይል መስጫ መሳሪያዎችን ማግኘታቸው በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

## ህጻናት ልጆች

የልደት ምዝገባ፡- የአንድ ህጻን ዜግነት የሚገኘው ከወላጆቹ ነው፡፡ ህጻናት ሲወለዱ እንዲመዘገቡ ህጉ ያዝዛል፡፡ በሆስፒታሎች ውስጥ የሚወለዱ ህጻናት ተመዝግበዋል፤ ከሆስፒታሎች ውጭ የሚወለዱት አብዛኛዎቹ አልተመዘገቡም፡፡ በተለይ በገጠር አካባቢዎች እጅግ በጣም አብላጫ ቁጥር ያላቸው ህጻናት የሚወለዱት በቤት ውስጥ ነበር፡፡ በዓመቱ ውስጥ መንግስት ህጻናትን አለማስመዝገብ ህዝባዊ አገልግሎቶችን የሚያሳጣ መሆኑን በማስታወቅ የልደት ምዝገባዎችን ለመጨመር በ2009 ተጀምሮ የነበረው ዘመቻ ቀጥሏል፡፡

<u>ትምህርት፡-</u> ህጉ ትምህርትን የግዴታ አያደርገውም፡፡ የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ሁሉን አቀፍ እና ከክፍያ ነፃ ቢሆንም በተለይ በገጠር አካባቢዎች የሐገሪቱን ወጣቶች የሚያስተናግዱ በቂ ት/ቤቶች የሉም፡፡ የትምህርት ቤት አቅርቦቶች ወጪ ለብዙ ቤተሰቦች የማይታሰብ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስወጣ ነው፡፡ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት የምዝገባ ምጣኔ የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ለወንድ ልጆች 90 በመቶ እና ለልጃገረዶች 84 በመቶ እንደሆኑ ነበር ያመለከቱት፡፡

<u>ህጻናትን ማጎሳቆል፡-</u>የሕጻናት ጉስቁልና እና ጥቃት የተስፋፋ ነበር፡፡ እንጥል መቁረጥ፣ ጉሮሮ መቧጠጥ እና የወተት ጥርስ መንቀል በጣም ከተስፋፉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል ነበሩ፡፡ በህጻናት ላይ የወሲብ ጥቃት በመፈፀም ተግባር ላይ መንግስት ቅጣት መጨመሩን በአፍሪካ ቻይልድ ፖሊሲ ፎረም የሚታተመው የ*2006 የህጻናት ደህንነት አፍሪካዊ ሪፖርት* አረጋግጧል፡፡ “ለህጻናት ደጋፊ የሆኑ” ችሎቶች በህጻናትና በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን አዳምጠዋል፡፡ በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንና በእምባ ጠበቂ ቢሮ ውስጥ የሴቶችና የሕጻናት ጉዳዮች ኮሚሽነር ነበር፡፡

<u>ያለ ዕድሜ እና የግዴታ ጋብቻ</u>፡- ህጉ ለሴቶችና ለወንድ ልጆች የጋብቻ እድሜ 18 ዓመት መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ ባለስልጣናት ይህንን ህግ በወጥነት የማያስከብሩ ሲሆን የገጠር ቤተሰቦችም አንዳንድ ጊዜ ድንጋጌው ስለመኖሩ ግንዛቤው የላቸውም። መንግስት ያለ ዕድሜ ጋብቻ ላይ መፍትሔ ለመስጠት የነደፈው ስልት ወንጀለኞችን ከመቅጣት ይልቅ ትምህርት በመስጠትና በማስታረቅ ላይ ነበር ያተኮረው። ለተጨማሪ መረጃዎች አባሪ “ሐ”ን ይመልከቱ።

<u>በህጻናት ላይ የሚፈፀም ወሲባዊ ብዝበዛ፡-</u> ወሲብን በስምምነት ለመፈፀም የተቀመጠው አነስተኛ ህጋዊ የእድሜ መጠን 18 ዓመት ቢሆንም ባለስልጣናት ይህንን ህግ አላስከበሩም፡፡ ለአቅመ ሄዋን/አዳም ካልደረሱ ህጻናት ጋር የወሲብ ግንኙነት በሚፈፅም ላይ ህጉ ከሶስት እስከ 15 ዓመት እስር ይደነግጋል፡፡ ለአቅመ ሔዋን/አዳም ባልደረሱ ልጆች የሚፈፀሙ የወሲብ ግንኙነቶችን የሚያሳዩ የብልግና ፅሑፎችን እና ስዕሎችን በሚያዘዋውሩ ላይ ህጉ የአንድ ኣመት እስርና የ10,000 ብር (346 ዶላር) መቀጮ ይደነግጋል፡፡ ህገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ዕድሜያቸው 11 ዓመት የሆኑ ሴት ልጆችን በሴተኛ አዳሪ ቤቶች እንዲሰሩ ይመለምላሉ፡፡ ወጣት ልጃገረዶች ከገጠር ወደ ከተማ እንዲዘዋወሩ እየተደረጉ በሆቴሎች፣ በቡናቤቶች በመዝናኛ (በሪዞርት) ከተማዎች እና በገጠር የጭነት መኪና መናህርያዎች ላይ በሴተኛ አዳሪነት እንዲሰማሩ ተደርገው ይበዘበዛሉ።

<u>ጨቅላ ህጻናትን መግደል ወይም የአካል ጉድለት ያለባቸውን ጨቅላ ህጻናት መግደል</u>፡- የአካል ጉድለት ያለባቸውን ጨቅላ ህጻናት ጨምሮ በሐይማኖታዊ ስርዓት እና በባዕድ አምልኮ ላይ የተመሰረተ የጨቅላ ህጻናት ግድያ ራቅ ባሉ የጎሳ አካባቢዎች በተለይም በደቡብ ኦሞ የቀጠለ ተግባር ነው፡፡ የአካባቢው መንግስታት ይህን ልማድ እንዲያስቀሩ ማህበረሰቦችን ለማስተማር ጥረዋል፡፡

<u>ተፈናቃይ ልጆች፡-</u> በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር የ2003 ሪፖርት መሰረት ወደ 150ሺህ ልጆች በጎዳና ላይ ኖረዋል፡፡ ከነርሱ መሀከል 60ሺህ ያህሉ በዋናው ከተማ ውስጥ ነበሩ፡፡ ወላጆች በሚያጋጥማቸው ህመም ወይም በቂ ባልሆነ የቤተሰብ ገቢ ምክንያት ልጆችን መርዳት አለመቻላቸው ችግሩን እንዳባባሰ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ይገልጻል፡፡ ፈጣን የከተማ መስፋፋት፣ ህገ ወጥ የስራ ቅጥር ደላሎች፣ በከተሞች ውስጥ የተሻለ ኑሮ የማግኘት ከፍተኛ ተስፋ እና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት በችግሩ ላይ ተጨማሪ እክል መፍጠራቸውን በ2007 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተደረገው ጥናት ያስገነዝባል፡፡ እነዚህ ልጆች አብዛኛውን ጊዜ ይለምናሉ፣ አንዳንዴ የወሮ በላ ቡድን አካል ይሆናሉ ወይም ህጋዊ ባልሆነ የስራ ዘርፍ ይሰማራሉ፡፡

የኦሮሚያ ክልል የሴቶች፤ የወጣቶች፤ እና የሕጻናት ጉዳይ ቢሮ እና የአካባቢው ፓሊስ በሃምሌ ወር 31 በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሕጻናት በሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባ እንደሆኑ የሚያሳይ ረፓርት አቅርበዋል፡፡ በዚያው ዘመን በምዕራብ እና ምስራቅ ወሊጋ ሕጻናት በሕገ ወጥ ዝውውር እንደሚሰለቡ ኢጋር ተከላካዮቻችን የዘገቡ

ሲሆን እነዚህ ሕገ ወጥ አዛዋዋሪዎቹ አገር ውስጥ በተፈናቀሉ ሕጻናት ላይ ለማነጣጠር መረባቸውን እንደጣሉ ያምናሉ፡፡

<u>በተቋም ውስጥ ያሉ ህጻናት፡-</u> በዩኒሴፍ በታተመው ስታቲስቲክስ መሰረት በ2004/2005(2012) በሐገሪቱ ውስጥ 4.5 ሚሊዮን፣ ማለትም ከህዝቡ 4.9 በመቶ የሚሆኑ ወላጅ አልባ ልጆች እንደነበሩ ተገምቷል፡፡ እጅግ ብዙዎቹ ከዘመድ አዝማድ ጋር ኖረዋል፡፡ መንግስታዊና በግል የሚንቀሳቀሱ የወላጅ አልባ ህጻናት ማሳደጊያዎች ከመጠን በላይ የተጣበቡ ሲሆኑ ሁኔታዎችም ብዙውን ጊዜ ንጽህና የጎደላቸው ነበሩ፡፡ በተቋም ውስጥ ያሉ ልጆች በቂ የጤና እንክብካቤም አላገኙም፡፡

<u>አለምአቀፍ የሕጻን ልጅ ጠለፋዎች/አፈናዎች</u>፡- ሐገሪቱ በአለምአቀፍ የህጻን ልጅ ጠለፋ ሲቪላዊ ገጽታዎች ላይ የ1972 (1980) የሄግ ስምምነት አባል አይደለችም፡፡. *በአለምአቀፍ በወላጅ የሕፃናት ጠለፋ ላይ የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ዓመታዊ ሪፖርት ይመልከቱ፡፡* https://travel.state.gov/content/travel/en/International-Parental-Child-Abduction/for-providers/legal-reports-and-data/reported-cases.html.

**ፀረ-ሴማዊነት**

የአይሁድ ማህበረሰብ ወደ 2,000 ሰዎች እንደነበሩ ይገልፃል፡፡ ፀረ-ሴማዊ ድርጊቶች ስለመፈፀማቸው ሪፖርቶች አልነበሩም፡፡ የአዲስ አበባ የአይሁድ ማህበረሰብ እምነቱን ለመተግበር የመንግስት ከለላ እንዳለው ማመኑን ሪፖርት አድርጓል፡፡ ነገር ግን የተወሰነ ማህበረሰባዊ መገለል ገጥሞታል፡፡

**የሰዎች ህገ-ወጥ ዝውውር**

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን *የሰዎች ህገ-ወጥ ዝውውር ሪፖርት ይመልከቱ፡፡* https://www.state.gov/trafficking-in-persons-report/.

**የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች**

ህገ መንግስቱ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የእኩል መብቶች አደራ/ሃላፊነት አይሰጥም፡፡ አካላዊ እና አእምሮአዊ ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በስራ ቅጥር ረገድ አድሎዎ እንዳይደረግባቸው ህጉ የሚከለክል ሲሆን፣ በህንጻ ውስጥ ላሉ አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲያገኙ መመሪያ ይሰጣል፤ ነገር ግን የአእምሮ ወይም የስሜት ህዋሳት ጉዳቶችን በግልጽ አይጠቅስም፡፡ መስማት ለተሳናቸው ሰዎች መኪና መንዳት ህገ ወጥ ነው። ህገ መንግስቱ እንዳስቀመጠው፤ “መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን፤ የአካል እና የአእምሮ አካለስንኩል ለሆኑ፤ ዕድሚያቸው ለገፉ፤ ወላጅ ወይም ጠባቂ አልባ ለሆኑ ሕጻናት ማገገሚያ እና እርዳታ ያቀርባል”። ይህ ድንጋጌ በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊ፤ እና በባህላዊ መብቶች ሥር ሲሆን፤ ይህም እኩል መብቶችን የሚሰጥ ሳይሆን አቅም በፈቀደ ሃብቶችን የሚመድብ ነው።

ህጉ በአካል ጉዳተኝነት ላይ የተመሰረተ የስራ ቅጥር አድሎን የሚያግድ ሆኖ አዎንታዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የሚያስገድድ ነው። በተጨማሪም የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰራተኞች ተገቢ የሥራና የስልጠና ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማቴሪያሎችን የማቅረብ ሃላፊነት የአሰሪዎች እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ሠራተኛ በሚቀጠርበት ጊዜ አካለ ስንኩል የሆነ ግለሰብ መስፍርቶቹን ካሟላ ወይም ከሌሎች እጩዎች እኩል ነጥብ ካስመዘገበ ለአካለስንኩሉ የቅጥር ቅድሚያ መሰጠት አለበት፡፡ በተጨማሪም ለአካል ጉዳተኞች ተገቢ የሆነ ትብብር፤ የሥራ ወይም የስልጠና ሁኔታዎችን እና ቁሳቁሶችን አሠሪዎች እንዲያመቻቹ ሃላፊነት ይጥልባቸዋል፡፡

ሕጉን በሥራ ላይ አላውልም የሚልን አሠሪ ሕጉ ከ2,000 እስከ 5,000 ብር($69 እስከ $173) ያስቀጣል፤ ይህም በአካለስንኩልና ምክንያት የሚደርስን መድሎ ሕጉ የመከላከል አቅሙን ዜሮ ያደርገዋል፡፡

ሕጉን ለመተግበር መንግስት ውስን እርምጃዎችን ነው የወሰደው። ለምሳሌ ያህል፤ መስማት ለተሳናቸው ሲቪል ሠራተኞች አስተርጎሚዎችን በመመደብ፡፡ አካለ ስንኩል ለሆኑ ግለሰቦች የቅጥር ሕጎቹን በሚመለከት የሚቆጣጠረው በሠራተኞች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕዝብ ግልጋሎት አስተዳደር ኮሚሽን ስር ነው፡፡

አካለ ስንኩል ለሆኑ ግለሰቦች ሕጉ ማንኛቸውም የሕዝብ ሕንጻዎች ተደራሽነትን የጠበቁ እንዲሆኑ ያስገድዳል፣ ቢሆንም ግን የሚያስከብር ዘዴ የለውም፡፡ ይህ ስለ ተደራሽነት የሚጠቅሰው አንቀጽ የሚገልጸው የአካል ስንኩላን ስለሆኑት ብቻ ሲሆን፤ የግንዛቤም ወይም የስሜትን ጉድለት አያካትትም፡፡ ህጉ ምንም እንኳ የተደራሽነት ደረጃዎችን የሚወስኑ ልዩ ደንቦች ባይኖሩትም የአካል ጉድለት ላለባቸው ሰዎች የህንጻ ተደራሽነትን እና የንጽህና ቤት አገልግሎቶች ተደራሽነትን እንዲያገኙ ይፈቅዳል፡፡ ህንጻዎችና የንጽህና ቤት አገልግሎቶች አብዛኛውን ጊዜ በአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አልነበሩም፡፡ የአካል ጉድለት ላለባቸው ሰዎች በህንፃ የምድር ቤት ወለል (ግራውንድ ፍሎር) ላይ የመኖሪያ ምርጫ እንዲሰጡ የንብረት ባለቤቶች የሚታዘዙ ሲሆን፣ አብዛኛውን ይህንኑ ይፈጽማሉ።

በተመድ የስነ-ህዝብ ፈንድ እና የስነ-ህዝብ ካውንስል ሪፖርት መሰረት የአካል ጉድለት ካለባቸው ሶስት ልጃገረዶች አንዷ ቢያንስ አንድ የወሲብ ጥቃት ይገጥማታል፡፡ በተጨማሪም በቤታቸውና በማህበረሰባቸው ውስጥ ስልታዊ እና ነውጥ የተሞላበት እንግልት ይገጥማቸዋል፡፡ ብዙዎቹ ለየት ያሉ በመሆናቸው እንደሚነቀፉ እና በጥንቆላ መተት ስር ተደርገው ስለሚታዩ እንደሚፈሩ ሪፖርቱ ይገልፃል፡፡

የአካል ጉዳት ያለባቸው ሴቶች በትምህርትና በስራ ቅጥር ተጨማሪ የከፉ እድሎች ይገጥሟቸዋል፡፡ በ2010 *(2002/2003) የስነ-ህዝብ ካውንስል የወጣት አዋቂዎች የቅኝት ጥናት መሰረት*፣ የአካል ጉድለት ከሌለባቸው 48 በመቶ ልጃገረዶችና 55 በመቶ ወንድ ልጆች ጋር ሲነፃፀሩ በትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩት የአካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች 23 በመቶ ነበሩ፡፡ በተጨማሪም የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጃገረዶች የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ልጃገረዶች ይበልጥ አካላዊና ወሲባዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡

በብሔራዊ ደረጃ መስማትና ማየት ለተሳናቸው ሰዎች በርካታ ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን፣ የአእምሮ(ኢንተሌክቹዋል) ጉዳት ላለባቸው ልጆችና ወጣቶች በርካታ የሥልጠና ማዕከላት አሉ፡፡ ከዘጠኙ የክልል መንግስታት ውሰጥ በአምስቱ የሰው ሰራሽ ጥርስና የአጥንት ህክምና ማዕከላት ኔትወርክ አለ።

የሠራተኞች ጉዳይ ሚኒስቴር ከአካለ ስንኩልና ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጉዳዮች በማስተናገዱ አካለ ስንኩል የሆኑ የሕዝብ ሠራተኞች በሥራ ላይ መድሎ እንዳይደርስባቸው ሥራ ቦታ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲሟሉላቸው ያዛል፡፡

**ብሔራዊ/ የዘር/የጎሳ አናሳ ማህበረሰቦች**

ሐገሪቱ ከ80 በላይ የብሔር ቡድኖች ያላት ሲሆን፣ከህዝቡ ወደ 34 በመቶ የሚሆነው ኦሮሞ ትልቁ ብሔር ነው፡፡ የፌዴራሉ ስርዓት በኢሕአዴግ የመጀመሪያ የአገዛዝ ዘመን ወቅት ትልልቅ የብሔር ቡድን መስመሮችን ተከትሎ ድንበሮችን አስምሯል፣ የወቅቱንም ህገ መንግስት አርቅቋል፡፡ ገዢው ፓርቲ እና ከትልልቆቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ አንዱ በበርካታ ብሔሮች ቅንጅት ላይ የተመሰረቱ ፓርቲዎች ቢሆኑም አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀዳሚነት በብሔር ላይ የተዋቀሩ ናቸው፡፡

በመስከረም 2011 በቡራዩ እና አካባቢው ከተሞች ላይ በብሄር የተነሳሳ አመጽ አስነስተዋል ባላቸው 109 ግለሰቦች ላይ በጥር ወር የፌዴራል አቃቢ ሕግ ክስ መስርቶ ነበር፡፡ በሪፓርቱ መሰረት ፓሊስ 81 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር አውሎ ቀሪዎቹን በመፈለግ ላይ ይገኛል።

ማንነታቸው ያልታወቀ አጥቂዎች በመስከረም 2011 በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ ተኩስ ከፍተው አራት የደህንነት ሠራተኞችን ገድለዋል፡፡ ይህም አጋጣሚ በክልል ውስጥ በሚገኘው ካማሺ ዞን ውስጥ በኦሮሞ እና በአማራ ብሄሮች ላይ ማንነትን የተመረኮዘ ጥቃት እንዲፍጸም አነሳሽ ሆኖ፤ ቢያንስ 67 ግለሰቦች ተገድለው በመቶ እና በሺ የሚቆጠሩ ተፈናቀሉ፡፡ ሪፓርቶች እንደሚጠቁሙት ወንጀሉን የፈጸሙት የኦነግን ባንዲራ ይዘው ነበር ተብሏል። ቢሆንም ግን የኦነግ ባለሥልጣኖች በዚህ ሁኔታ ውስጥ ተሳትፎ የለንም ብለው ይከዳሉ።

የአማራ ክልል ፓሊስ ግንቦት 17 ተማሪ ገድለዋል ያላቸውን የተጠረጠሩ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን በሰኔ ወር ውስጥ በቁጥጥር ስር አውሎ ነበር፡፡ የአካባቢው ዜና ዘጋቢዎች እንደገለጹት፤ ከትግራይ ክልል የመጣን ተማሪ አጥቂዎቹ ደብድበው ነው የገደሉት፡፡ ሁለቱም የአማራ እና የትግራይ ክልሎች በጊዜው ግድያውን አውግዘው ይህን ድርጊት የፈጸሙትን ለፍርድ ለማቅረብ ቃል ገብተዋል፡፡ ብሄሩ አማራ የሆነ የአክሱም ዩኒቨርስቲ ተማሪ ግንቦት 27 በትግራይ ክልል ውስጥ ተገደለ፤ ብዙዎች ደብረ ማርቆስ ለደረሰው ግድያ አፀፋ ነው ብለው ይገምታሉ። በብሄር ምክንያት የተፈጸመውን ግድያ የትግራይ ክልል አውግዞ ድርጊቱን የፈጸሙትን ለፍትህ ለማቅረብ በጊዜው የሚችለውን ሁሉ እንደሚያደርግ ገልጿል።

## በወሲብ ዝንባሌና በጾታ ማንነት ላይ የተመሰረቱ የጥቃት የማግለልና ሌሎች የማጎሳቆል ተግባራት

በስምምነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ጾታ ወሲባዊ ተግባር ህገ ወጥ የሆነና ከሶስት እስከ 15 ዓመት እስር የሚያስቀጣ ነው፡፡ ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች (LGBTI) ላይ የሚደረግን ማግለል የሚከለክል ህግ የለም፡፡ ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች ላይ ጥቃት መፈፀምን የሚያሳዩ ሪፖርቶች ነበሩ፣ ይሁን እንጂ ብቀላን፣ ማግለልን ወይም መጠቋቆምን በመፍራት ሪፖርት የማድረግ ሁኔታ ውሱን ነበር፡፡ ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ምርመራን በመደገፍ ረገድ የጥላቻ ወንጀል ህጎች ወይም ሌሎች ስለወንጀል ፍትሕ የአሰራር ዜዴዎች የሉም፡፡ ግለሰቦች በከባድ ማህበረሰባዊ መጠቋቆምና በስምምነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ፆታ ወሲባዊ ተግባር ህገ ወጥነት ምክንያት ሴት ከሴት ወሲብ ፈጻሚዎች፣ ግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ያላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ያስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ያላቸው ሰዎች በአብዛኛው ራሳቸውን አይገልጹም፡፡የሴት ከሴት ጋር ወሲብ ፈጻሚዎች፤ የግብረሰዶማውያን፡ የባለ ሁለት ፆታ ፍናፍንቶች፤ የፆታ ቀያሪዎች እና የህብረት ፆታ ፈፃሚዎች ማህበረሰብ አቀንቃኞች/አክቲቪስቶች ክትትል እንደሚደረግባቸው ሪፖርት አድርገው ለደህንነታቸው እንደሚፈሩ ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ ጾታ የወሲብ ተግባራት ውስጥ በመሳተፋቸው የታሰሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች ስለመኖራቸው የሚገልጹ ሪፖርቶች የሉም።

አዲስ አበባ ያለው የኤይድስ ሪሶርስ (ግብዓት) ማዕከል ራሳቸውን ግብረሰዶማዊ ወይም ሴት ከሴት ጋር ወሲብ የሚፈፅሙ አድርገው የገለፁ እና አብዛኞቹ ወንዶች የሆኑ የስልክ ደዋዮች ባህርያቸውን በመለወጥ መገለልን ለማስቀረት ድጋፍ መጠየቃቸውን ሪፖርት አድርጓል፡፡ ብዙዎች ግብረሰዶማዊያን መበርገግ ፣ ግራ

መጋባት፣ የማንነት ቀውስ፣ ጭንቀት፣ ራስን ማግለል፣ ሐይማኖታዊ ግጭትና ራስን የማጥፋት ሙከራዎች እንደገጠማቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡

በግንቦት እና ሰኔ ቶቶ አስንብኚ፤ ግብረ ሶዶማዊ ማህበረሰቡን ለማገልገል ትኩረት ሰጥቶ የሚንቀሳቀስ ቺካጎ ከተማ ያለ አስንብኚ ድርጅት በጥቅምት ወር ለ16 ቀናት የሚቆይ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ታዋቂ ስፍራዎችን ለማስንብኘት የ "ኢትዪጵያ ቅርሶች" በሚል ስያሜ ያዘጋጀው የጉብኝት ማስታወቂያ መጠነ ሰፊ የሆነ ተቃውሞ አጋጥሞታል፡፡ እንደ ድርጅቱ አባባል፤ በውጪ አገራት ድረገጽ ላይ ያየሁትን የዛቻ እና የጥላቻ መልዕክቶች ብዛት ግንቦት 18 በሪፖርት መልክ እንዳወጣ ገፋፍቶኛል ይላል። ተራ ዜጎች ሰኔ 2 አዲስ አበባ ውስጥ ፀረ ሶዶማዊ ሰልፍ እንዲደረገ ጠይቀው የነበር ቢሆንም ሰልፉች ግን አልተካሄዱም፡፡እናም ጎብኚዎች ሊደርሱባቸው የሚችሉትን አደጋዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ድርጅቱ እቅዱን ለመሰረዘ ተገደደ፡፡

### ሌሎች ማህበረሰባዊ ጥቃቶች ወይም ማግለሎች

በአለምአቀፍ የስደተኞች ድርጅት የመፈናቀል መከታተያ ማትሪክስ መሰረት፣ አብዛኞቹ መፈናቀሎች በጁን (በሰኔ) ወር ያጋጠሙ ሲሆን በኦሮሚያ ክፍሎች በደቡብ ብሄርበ ብሔሮች መካከል የተከሰተው ግጭት በደብብሕ ጌዲኦ ዞን እና በኦሮሚያ ምዕራብ ጉጂ ዞን ወደ አንድ ሚሊየን ለሚጠጉ ነዋሪዎች የነበሩባቸውን አካባቢዎች እንዲለቁ ምክንያት ሆኗል።

### ኤችአይቪ እና ከኤድስ ጋር የተገናኘ አጉል መሃበራዊ ምልክት

በኤችአይቪ/ኤድስ በተጠቁ ሰዎች ላይ የሚያጋጥሙ አጉል ማህበራዊ ምልክት እና መገለል በትምህርት፣ በቅጥር፣ እና በማህበረሰብ ውህደት ዙሪያ ቀጥለዋል። በኤችአይቪ/ኤድስ የተጠቁ ሰዎች ወደ በርካታ አገልግሎቶች ለመዳረስ መቸገራቸውን ሪፖርት አድርገዋል። በችግሩ መጠን ላይ አሀዛዊ መረጃዎች የሉም።

### ሌላ ማህበራዊ ሁከት ወይም ማግለል

አማራ ክልል ውስጥ ለጎንደር ከተማ ቅርብ በሆኑ ብዙ መንደሮች ላይ የካቲት 1 የቅማንት ጎሳ በሆኑ የታጠቁ ቡድኖች ጥቃት ደረሰ። የአማራ ክልል ባለሥልጣኖች እንዳሳወቁት 300 የሚሆኑ አጥቂዎች 300 ቤቶችን አውድመው 30 ግለሰቦችን ገድለዋል፡፡ ሪፓርቶች እንደሚያሳዩት ይህ አመጽ ቢያንስ 50,000 ሰዎች ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ አድርጓል። የአማራ ክልልም የተፈናቀሉትን ሰዎች ለማስተናገድ አቅም ያንሰኛል ሲል ለፌዴራል መንግሥት አሳወቀ። የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሃይል ከአመጹ ጋር ግንኙነት አላችሁ በማለት 138 ግለሰቦችን ሰሜን ጎንደር ውስጥ በቁጥጥር ስር አዋለ። ፓሊስ 37 ተጠርጣሪዎችን በግድያ እና 101 ተጠርጣሪዎችን በጥቃቱ ወቅት በተካሄዱ ዝርፊያዎች ወንጅሏል፡፡ የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሃይል ከታሰሩት ሰዎች በሮኬት የሚውዘገዘጉ ቦምቦችን ጨምሮ ሌሎች መሳሪያዎችን ይዘዋል።

የሕዝብ ዩኒቨርስቲዎች በብሄር ውጥረቶች የተቀጣጠለ አመጽ ያዩ ሲሆን ይህም በከፍተኛ ሁኔታ የትምህርት ዓመቱን አቋርጦታል።

## ክፍል 7፡ የሰራተኛ መብቶች

### ሀ. የመደራጀት ነጻነት እና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብት

ህገ መንግስቱ እና ህጉ ከመንግስት ሰራተኞችና በቀዳሚነት በመንግስት ዘርፍ ውስጥ ካሉ አንዳንድ የሰራተኞች ምድቦች በስተቀር ማህበራትን የመመስረትና አባል የመሆን፣ ህጋዊ የስራ ማቆም እንዲሁም ሕጋዊ አድማ የማድረግና የህብረት ድርድር የማካሄድ መብትን ለሰራተኞች ይሰጣሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሌሎች ድንጋጌዎችና ህጎች እነዚህን መብቶች በጣም ይገድባሉ፡፡ በተለይም ህጉ የአስተዳደር ሰራተኞችን፣ አስተማሪዎችን፣ የጤና እንክብካቤ ሰራተኞችን፣ ዳኞችን፣ አቃቤ ህጎችን፣ የደህንነት አግልገሎት ሰራተኞችን፣ የቤት ሰራተኞችን እና በወቅት ላይ የተመሰረተ የግብርና ስራ የሚያካሄዱ ሰራተኞችን በማህበራት መደራጀትን ይከለክላል፡፡ የጸረ-ማህበር ማግለልን በመፈፀም ጥፋተኛ የሆኑ አሰሪዎች በማህበር የስራ እንቅስቃሴዎች ምክንያት የተሰናበቱ ሰራተኞችን ወደ ስራ ገበታቸው እንዲመልሱ ህጉ የሚያስገድድ ሲሆን በአብዛኛው ይህንን አድርገዋል።

አንድን ማህበር ለመመስረት ቢያንስ 10 ሰራተኞች ያስፈልጋሉ፡፡ ባለፉት 10 አመታት ውስጥ የማህበር መሪ ከፖለቲካ ጋር ነክኪ በሌለው ወንጀል ከተከሰሰ ህጉ ምዝገባን ሊከለክል ይችላል። በዚህ ላይ ተመስርቶ የተከለከለ ምዝገባ መኖሩን የሚያሳዩ ሪፖርቶች አልነበሩም። መንግስት የአንድን ማህበር ምዝገባ በራሱ የአንድ ወገን ውሳኔ ብቻ ለመሰረዝ ይችላል፡፡ ሰራተኞች በእያንዳንዱ የስራ ቅጥር ሳቢያ ከአንድ በላይ የሰራተኛ ማህበር አባል ለመሆን አይችሉም፡፡ የሰራተኛ ማህበር ድርጅት በገሃድ ፖለቲካዊ ሁኔታ ውስጥ መስራት እንደሌለበት ህጉ ይደነግጋል፡፡ የፖለቲካ ተግባር በመሳሰሉ የተከለከሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሰማራት ምክንያት የአስተዳደር ባለስልጣናት የማህበሩን ምዝገባ ለመሰረዝ ፍ/ቤት እርምጃዎች አማካኝነት ጠይቀው እርዳት እንዲያገኙ ህጉ ይፈቅዳል፡፡

ህጉ ለሕብረት ድርድር መብት እውቅና ቢሰጥም፣ ይህ መብት በህጉ መሰረት በጥብቅ ተገድቧል፡፡ የጋራ ድርድር ስምምነትን ለማሻሻል ወይም ለመተካት ያለሙ ድርድሮች ጊዜው ባበቃ በሶስት ወራት ውስጥ መከናወን አለባቸው፣ አለበለዚያ በምንዳዎች እና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች ላይ የበፊቶቹ ድንጋጌዎች መተግበራቸው ያቆማል፡፡ የድርጅት ማህበራት በፋብሪካ/ኢንዱስትሪ ደረጃ ብቻ በምንዳ ክፍያ ላይ እንዳይደራደሩ ያግዳል፡፡ የመንግስት ት/ቤት አስተማሪዎችን ጨምሮ የመንግስት ሰራተኞች በተቀጣሪ ሰራተኞች የተቋቋሙ የሙያ ማህበራትን የመመረስትና አባል የመሆን መብት ቢኖራቸውም የሕብረት ድርድር ማድረግ አይችሉም፡፡ በመንግስት ዘርፍ ውስጥ የግልግል (አርቢትሬሽን) የአሰራር ሥርአቶች ከግሉ ዘርፍ ይልቅ የበለጠ አጋጅ ናቸው፡፡ ሕጉ የሰራተኞች ወይም የአሰሪዎችን ድርጅቶች በመመስረት፣ በማካሄድ ወይም በማስተዳደር ረገድ በሌሎች አካላት በሚደረጉ የጣልቃ ገብነት ተግባራት ላይ ፍቱንና በቂ ቅጣቶች አይደነገግም፡፡

ሰራተኞች ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ ህገ መንግስቱና ህጉ ቢደነግጉም ህጋዊ ስራ የማቆም አድማ ተግባራትን በሚያግድ መልኩ አስቸጋሪ የሚያደርጉ በጣም ውስብስብና ጊዜ የሚፈጁ ፎርማሊቲዎችን የሚያዙ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይይዛል፡፡ ተበዳይ ሰራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በፊት ከአሰሪዎች ጋር ለመታረቅ እንዲሞክሩ ህጉ የሚያዝ ሲሆን ረዥም የክርክር እልባት መስጫ ሂደትን ያካትታል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች አሰሪዎች ሰራተኞችን ወደ መስሪያ ቤት እንዳያስገቡ ባላቸው መብት ላይም በእኩል ደረጃ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ ፈቃድ ላለው የስራ ማቆም አድማ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ሁለት ሶስተኛው እንዲህ አይነቱን እርምጃ መደገፍ አለባቸው፡፡ ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ወይም ወደ አሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቶች ቦርድ ካልተመራ፣ ማህበሩ ወደ እነዚህ ሁለት አማራጮች መሄድ ሳያስፈልገው የስራ ማቆም አድማ የማድረግ መብትን ይይዛል፣ ይህ የሚሆነው ግን ለሌላው ወገን እና ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢያንስ የ10 ቀናት ማሳሰቢያ ከሰጡና በእርቅ ጉዳይ ላይ ጥረቶች ካደረጉ ነው፡፡

በተጨማሪም ህጉ የአየር ትራንስፖርትና የአውቶብስ አገልግሎቶችን፣ የኤሌክትሪክ ሐይል አቅራቢዎችን የነዳጅ ማደያ ሰራተኞችን የሆስፒታልና ፋርማሲ ሰራተኞችን፣ የእሳት አደጋ ተከላካዮችን፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ሰራተኞችንና የከተማ ውስጥ የጽዳት ሰራተኞችን ጨምሮ መሰረታዊ አገልግሎቶች በሚሰጡ ሰራተኞች የሚደረጉ የስራ ማቆም አድማዎችን ያግዳል፡፡ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ዝርዝር የዓለምአቀፍ ሰራተኞች ድርጅት (ILO) ስለ መሰረታዊ አገልግሎቶች ከሰጠው ፍቺ አልፎ የሚሄድ ነው፡፡ በአድመኞች ላይ ብቀላ እንዳይደረግ ህጉ ቢከለክልም ያልተፈቀዱ የስራ ማቆም እርምጃዎች በማካሄዳቸው ጥፋተኛ በሆኑ ማህበራትና ሰራተኞች ላይ የፍትሐብሔርና የወንጀል መቀጫዎችን ጭምር ይደነግጋል፡፡ የወንጀለኛ መቅጫው ህግ ድንጋጌዎች ተጨማሪ ክብደት ያላቸው መቀጫዎችን የሚያዙ ከሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ የተተረጎመው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ መንግስትን፣ ህዝብን ወይም የግል ጥቅሞችን በሚጎዳ ሁኔታ የሥራ ማቆም አድማ የሚያደርግ፣ ሌሎችን አድማ እንዲያደርጉ የሚገፋፋ ወይም ስራውን በትክክለኛ ሁኔታ የማያከናውን ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የጉልበት ስራን የመስራት ግዴታ ለሚያካትት እስር ተገዢ ይሆናል፡፡

የሠራተኛ መብቶችን የሚጠብቁትን ሕጎች መንግሥት አጥብቆ አላስፈጸመም፡፡ ሕጉ ፀረ ማህበር መድሎን ቢከለክልም፤ አሰሪዎች የማህበራትን እንቅስቃሴ እንደሚያቆርጡ ማህበራቱ ሪፓርት አደርገዋል። አድማ የሚያካሂዱ ላይ በቀል እንዳይወሰድ ይከለክላል፤ ቢሆንም ግን ባለሥልጣናት ዘጠኝ የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪውች አድማ ስለ አደረጉ አስረዋቸው ነበር፡፡ መንግሥት አግባብነት ያላቸውን ሕጎች አበክሮ አላስከበረም፤ ጥሰቶችን ለማስወገድ ቅጣቶቹ በቂ አይደሉም፡፡ መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ፤ የቤት ሰራተኞችንና በወቅት ላይ የተመሰረተ የግብርና ስራ የሚሰሩ ሰራተኞችን ጨምሮ መደበኛ ያልሆነ የጉልበት ስራ ዘርፍ በማህበር አይደራጅም ወይም በአሰሪና ሰራተኛ ህጎች ከለላ አይሰጠውም፡፡ ህጉ ሰራተኞችን በስራ ቅጥር ግንኙነት ውስጥ እንዳሉ ሰዎች ይተረጉማቸዋል፡፡ የሠራተኞች በበቂ ሁኔታ አለመኖር መንግስትን የህግ ከለላ ላገኙ ዘርፎች ተፈጻሚ ህጎችን በስኬት ከማስከበር አግዶታል፡፡ የፍ/ቤት የአሰራር ሥርዓቶች ብዙውን ጊዜ ለተራዘሙ መዘግየቶችና ይግባኞች ተገዢ እየሆነ ነው፡፡ ከፍተኛ የሥራ አጥነት፣ የብቀላ ፍራሐት እና የአሰሪና ሰራተኛ ክሶችን ችሎት ለመስማት የሚያጋጥሙ የተንዛዙ መዘግየቶች ሰራተኞችን በስራ ማቆም አድማዎች ወይም በሌሎች የሰራተኛ እርምጃዎች ከመሳተፍ እንዳገዳቸው የአሰሪና ሰራተኛ ሃላፊዎች ሪፖርት አድርገዋል፡፡

ሁለት ሶስተኛው የማህበር አባላት መንግሥት ከሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ የንግድ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች አካላት ናቸው።

ብዙ ጊዜ ሪፖርት ባይደረግም የፀረ-ማህበር እንቅስቃሴዎች ተከስተዋል፡፡ ሰራተኞች ማህበራትን እንዳይመሰርቱ አንዳንድ ትልልቅ የውጭ ኢንቨስተሮች በአብዛኛው አለመፍቀዳቸውን፣ የማህበር መሪዎችን ዘወትር ማዘዋወራቸውን ወይም ማሰናበታቸውን እና አባላት ማህበራትን ትተው እንዲወጡ ማስፈራራታቸውን እና ጫና መፍጠራቸውን የዘገቡ የሚዲያ ሪፖርቶች ነበሩ፡፡ በፍ/ቤቶች ውስጥ ባሉ የክስ ውዝፎች ምክንያት ህገ ወጥ የተባሉ የሥንብት ክሶችን ለመወሰን ብዙ ጊዜ ዓመታት ይወስዳሉ፡፡

## ለ. አስገዳጅ ወይም የግዴታ የጉልበት ስራ ክልከላ

ህጉ ሁሉንም ዓይነት የግዴታ ወይም አስገዳጅ የጉልበት ስራን የሚከለክልና በወንጀል የሚያስጠይቅ ቢሆንም ፍ/ቤቶች እንደ ቅጣት እርምጃ በማድረግ አስገዳጅ የጉልበት ስራን እንዲያዙ ይፈቅድላቸዋል። መንግስት በተሳካ ሁኔታ ህጉን ያላስከበረ በመሆኑ አስገዳጅ የጉልበት ስራ አጋጥሟል።

የፌዴራል መንግስት በ2007 በፀረ ህገ-ወጥ ዝውውር የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ላይ አጠቃላይ የጥገና ለውጥ እንዲተገበር አድርጓል። ባርነትን፣ በእዳ ምክንያት አገልጋይ አድርጎ መያዝን፣ በግዴታ በሴተኛ አዳሪነት ማሰማራትን እና በገባርነት መጨቆንን ጨምሮ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርንና ብዝበዛን በሚያካሄዱ ላይ ህጉ ከባድ ቅጣት ያዝዛል፡፡ መቀጫዎቹ በተለይ በጥቃት ላይ እየጨመረ ከሚሄደው የህግ ማስከበር ትኩረት ጋር ሲጣመሩ ድርጊቱን ለማገድ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በፌዴራልና በክልል ደረጃዎች ለሚገኙ ፖሊሶች በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና በብዝበዛ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡

ብዙውን ጊዜ በአስገዳጅ ድርጊት ስር ያሉ አዋቂዎችና ልጆች በጎዳና ላይ ንግድ፣ በልመና፣ በእጅ በሚሸመኑ የባህላዊ የሽመና ስራ ጨርቆች ወይም በግብርና ስራ ላይ ተሰማርተዋል፡፡ እንዲሁም ልጆች በአስገዳጅ የቤት ውስጥ የጉልበት ስራ ይሰራሉ፡፡ በእዳ ምክንያት በገባርነት የመያዝ ሁኔታዎች በይበልጥ በገጠር አካባቢዎች ውስጥ በባህላዊ ሽመና፣ በሸክላ ስራ፣ በከብት እረኝነት እና በሌሎች የግብርና ስራዎች ውስጥም ተሰማርተዋል።

መንግስት አንዳንድ ጊዜ እስረኞችን ከማረሚያ ቤቶች ውጭ ለግል ድርጅቶች እንዲሰሩ የሚያሰማራ ሲሆን፣ ይህንን ድርጊት የአለምአቀፍ አሰሪና ሰራተኛ ድርጅት እንደ አስገዳጅ የጉልበት ስራ መውሰድ ይቻላል ብሏል።

በhttps://www.state.gov/trafficking-in-persons-report/ ላይ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የሰዎችን ህገ-ወጥ ዝውውር ሪፖርት ጭምር ይመልከቱ፡፡

## ሐ. የሕፃናት የጉልበት ስራ ክልከላ እና አነስተኛው የሥራ ቅጥር እድሜ

ህጉ በጣም አስከፊ የሆኑ ማንኛቸውንም አይነት የሕፃን ልጅ የጉልበት ሥራ ይከለክላል፡፡ መንግስት አግባብነት ያላቸውን ህጎች በተሳካ ሁኔታ ያልተገበረ ሲሆን፣ መቀጫዎችም የህግ ጥሰቶችን ለማገድ በቂ አይደሉም፡፡

በህጉ መሰረት ለቀን ክፍያ ወይም ለደመወዝተኝነት አነስተኛ የስራ ቅጥር እድሜ 14 ዓመት ነው፡፡ አነስተኛ የእድሜ ድንጋጌዎች ግን በውለታ/በኮንትራት ለሚሰሩ ሰራተኞች ብቻ እንጂ እጅግ ብዙ የስራ ቅጥር ህፃናትን በሚያካትተው ለግላቸው በተቀጠሩ ወይም የማይከፈልበት ስራ በሚሰሩ ልጆች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡ እድሜያቸው ከ14 እስከ 18 የሆኑ ህጻናት አደገኛ ወይም የሌሊት ስራ መስራትን ህጉ ይከለክላል፡፡ የህጻን ልጅን ጤንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ማንኛውም ስራ እንደ አደገኛ ስራ ሆኖ በህግ ይተረጎማል፡፡ የተከለከሉ የሥራ ዘርፎች የመንገደኛ ማጓጓዣ ትራንስፖርትን፣ በኤሌክትሪክ ሐይል ማመንጫ ኢንዱስትሪዎች መስራትን፣ የፋብሪካ ስራን፣ ከመሬት ወለል በታች መስራትን፣ ጎዳና ማጽዳትን እና ሌሎች ብዙ ዘርፎችን ያካትታሉ፡፡ አደገኛ ተንቀሳቃሽ እና ሌሎች መሳሪያዎች አገልግሎት የሚሰጡበት ልማዳዊ የሽመና ሥራ የአደገኛ ሥራ ገደቦች ሽፋን አይሰጠውም። በአደገኛ ስራ ላይ ከተደረገው ክልከላ በመነሳት እድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በሙያ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መማርን ህጉ በግልጽ ያግዳቸዋል፡፡ ከ14 እስከ 18 እድሜ ያላቸው ልጆች በቀን ከሰባት ሰዓታት በላይ እንዲሁም ከምሽቱ 4፡00 እስከ ጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ወይም በበዓል ቀናት ወይም በእረፍት ቀናት እንዲሰሩ ህጉ አይፈቅድም፡፡

የሕጻናት የጉልበት ስራ ከባድ ችግር ሆኖ ዘልቋል (በተጨማሪ ክፍል 7.ለን ይመልከቱ) ፣እናም በርካታ ቁጥር ያላቸው ህጻናት በተከለከሉ፣ እና አደገኛ በሆኑ በተለይ በግንባታው ዘርፍ ይሰራሉ፡፡

የትምህርት ቤት የተማሪዎች ምዝገባ በተለይ በገጠር አካባቢዎች ዝቅተኛ ነበር። ትምህርት የመማርን አስፈላጊነት ለማጠናከር፣ ልጆች በዋናነት በግብርና ስራ በተሰማሩባቸው ማህበረሰቦች ላይ መያድ፣ መንግስታዊ እና ማህበረሰብ-አቀፍ የጋራ ግንዛቤ ማስጨበጫ ጥረቶች ትኩረት አድርገዋል፡፡ መንግስት

በግብርናው ዘርፎች ውስጥ የሕጻን ልጅ የጉልበት ስራ ችግርን ለመዋጋት የግብርና አሰራሮችን በማዘመንና ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ላይ መዋዕለ-ንዋይ አፍስሷል፡፡

ልጆች በገጠር እና በከተማ አካባቢዎች አዘውትረው በለጋ እድሜያቸው መስራት ይጀምራሉ፡፡ በተለይ ሕይወትን በማቆያ የግብርና ምርት ስራ፣ በባህላዊ ሽመና፣ በአሳ ማጥመድ እና በቤት ውስጥ ስራ የህጻን ልጅ የጉልበት ስራ ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡ ቁጥራቸው እያደገ የመጣው ልጆች በግንባታ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። በገጠር አካባቢዎች ያሉ ህጻናት በተለይም ወንድ ልጆች ከብት በማገድ፣ ጥቃቅን እቃዎችን በመሸጥ፣ በማጨድና አረም መንቀልን በመሳሰሉ ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉ ሲሆን ሴቶች ልጆች ደግሞ ማገዶ በመልቀም እና ውሃ በመቅዳት ላይ ተሰማርተዋል፡፡ ትንንሽ ልጆች ወርቅ የማምረት ስራ ይሰራሉ፡፡ በአነስተኛ ደረጃ በሚካሄድ የወርቅ ማዕድን ስራ የማዕድን ጉድጓዶችን ይቆፍራሉ እንዲሁም ከባድ የውሃ ጭነቶችን ይሸከማሉ፡ ወላጅ አልባ ልጆችን ጨምሮ በከተማ አካባቢዎች ያሉ ህጻናት በርካታዎቹ ብዙውን ጊዜ ለረጅም ሰዓታት የቤት ውስጥ አገልግሎት ስለሚሰጡ ትምህርታቸውን አዘውትረው እንዳይከታተሉ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም ልጆች በማምረቻ ቦታዎች፣ ጫማ በመጥረግ፣ ልብስ በመስፋት፣ መኪና በመጠበቅ፣ በህዝብ ትራንስፖርት፣ በጥቃቅን ንግድ፣ በተሸካሚነት እና የታክሲ ተራ በማስያዝ ይሰራሉ፡፡ አንዳንድ ልጆች በአነስተኛ ክፍያ ወይም ምንም ሳይከፈላቸው እና የስራ ላይ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች ሳይኖራቸው በአደገኛ ከባቢ-ሁኔታዎች ውስጥ ለረጅም ሰዓታት ይሰራሉ፡፡ ህጻናት የጉልበት ሰራተኞች አካላዊ፣ ወሲባዊ እና ስሜታዊ ጥቃትን የመሳሰሉ በደሎች በአሰሪዎቻቸው ይደርስባቸዋል፡፡

ህገ-ወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች ድህነት ከተንሰራፋባቸው የገጠር አካባቢዎች ልጃገረዶችን በመበዝበዝ በዋናነት በቤት ውስጥ የባርነት አገልግሎት እና በሐገሪቱ የወሲብ ንግድ ውስጥ ያሰማሯቸዋል፡፡

በhttps://www.dol.gov/agencies/ilab/resources/reports/child-labor/findings ላይ በጣም በከፉ የህጻን ልጅ ጉልበት ብዝበዛዎች ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የጉልበት ስራ ግኝቶችን ጭምር ይመልከቱ።

### መ. ከቅጥር እና ከሥራ ጋር የተያያዘ ማግለል

ህጉ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣በትዳር ሁኔታ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ ትስስር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በእርግዝና፣ በማህበረ ኢኮኖሚ ደረጃ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ ወይም በ "ማናቸውም ሌሎች ሁኔታዎች" ላይ ተመስርቶ የሚደረግ ማግለልን ይከለክሏል፡፡ቅጥርንና የሥራ አይነትን አስመልክቶ ህጉ ማግለልን ይከለክላል፣ ይሁን እንጂ ባለስልጣናት እነዚህን መብቶች ባልተመጣጠነ ሁኔታ ነው በስራ ላይ የሚያውሉት። ህጉ በእርጉዝ ሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ ላለ ተጨማሪ ጫና ልዩ እውቅናን ይሰጣል። ከላይ በተጠቀሱት ማናቸውም ምክንያቶች ላይ ለሚደረግ ማግለል የጥፋተኝነት መቀጫው ጥሰቶችን ለማስቆም በቂ አይደለም። መንግስት ህጉን ለማስከበር የተገደቡ እርምጃዎችን ነው የወሰደው፡፡ የወሲብ ዝንባሌ፣ የጾታ ማንነት እና የኤችአይቪ ተሸካሚ መሆን በህጉ መሰረት ከለላ ለማግኘት መሰረት የላቸውም።

በቅጥርና በሥራ ዓይነት ከወንዶች ይልቅ አነስተኛ የቅጥር እድል ባላቸው ሴቶች ላይ መገለል የሚያጋጥም ሲሆን፣ ስራዎች ቢገኙም ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ አይፈፀምም፡፡ በቅጥርና በሥራ ዓይነት ውስጥ የማግለል ሁኔታ በወሲብ ዝንባሌ፣ በፆታ ማንነት፣ ወይም በሁለቱም ላይ ይከሰታል።

በስደተኛ ሰራተኞችም ላይ የማግለል ተግባራት አጋጥመዋል፡፡

## ሰ. ቅቡልነት ያላቸው የስራ ሁኔታዎች

በብሔራዊ ደረጃ የተቀመጠ አነስተኛ የክፍያ ተመን የለም፡፡ አንዳንድ የመንግስት ተቋማት እና የመንግስት ድርጅቶች የራሳቸውን አነስተኛ ክፍያዎች ይወስናሉ፡፡ በቁጥር ከፍተኛ የደመወዝ ተከፋይ ቡድን የሆኑ የመንግስት ዘርፍ ሰራተኞች በወር ከድህነት መስመር በላይ የሆነ አነስተኛ ክፍያ ያገኛሉ። በአጠቃላይ መንግስት የክፍያ ህጎችን አጥብቆ በስራ ላይ አላዋለም፡፡

ህጉ ከ24 ሰዓት የእረፍት ጊዜ ጋር ቢበዛ የ48-ሰዓት ህጋዊ የስራ ሳምንት፣ ለትርፍ ጊዜ ስራ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈል፣ እና በግዴታ የሚሰራ ተጨማሪ የትርፍ ጊዜ ስራ እንዳይኖር ይደነግጋል፡፡ አሰሪዎች የትርፍ ሰዓት ስራን ለመጠቀም የሚችሉባቸው 4 ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነርሱም፡- የስራው አስቸኳይነት፣ አደጋ፣ የሰራተኛ መቅረት፣ እና የአማራጮች እጦት ናቸው፡፡ በተጨማሪ አሰሪዎች በቀን ከሁለት ሰዓታት፣ በወር ከ20 ሰዓታት እና በዓመት ከ100 ሰዓታት ለሚበልጥ ጊዜ ሰራተኞቻቸውን የትርፍ ሰዓት ስራ ማሰራት የለባቸውም፡፡ ህጉ በህዝብ ድርጅቶች እና በመንግስት የፋይናንስ ተቋማት የሚሰሩ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲያገኙ መብት ይሰጣቸዋል፤ የመንግስት ሰራተኞች ለትርፍ ሰዓት ስራ ማካካሻ የሚሆን የእረፍት ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡

መንግስት፣ ኢንዱስትሪዎች እና ማህበራት በብዙ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለሰራተኛ ደህንነት ሙሉ መፍትሔ በማይሰጡ የስራ ላይ ደህንነትና የጤና ደረጃዎች ላይ ይደራደራሉ፡፡ የቤት ሰራተኞችን እና በወቅት ላይ የተመሰረተ የግብርና ሰራተኞችን ጭምር የሰራተኞች ማህበር ከመመስረት በተለየ የህግ ሁኔታ ይከለከላሉ። በአጠቃላይ በስራ ቦታ ውስጥ ከጤና እና ከደህንነት ጥበቃ ደንቦች ጥቅም ይነፈጋሉ።

የአሰሪና ሰራተኞች ሚኒስቴር የኢንስፔክሽን መምሪያ የስራ ቦታ ደረጃዎችን የማስከበር ሃላፊነት ነበረበት። የሥራ ላይ ደህንነት እና የጤና እርምጃዎች በተጠናከረ ሁኔታ ስራ ላይ አልዋሉም። ሚኒስቴር መ/ቤቱ ደንብ የመከበር አፈጻጸምን ለመከታተል የሰራተኛ ቁጥጥርን ያካሄደ ቢሆንም መንግስት ህጉን ለማስከበር በቂ የተቆጣጣሪዎች ብዛት አልነበረውም። የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአስተዳደ ውሱንነት፤ ለመቀበል፣ ለመመርመር፣ እና የጥሰት ውንጀላዎችን ለመከታተል የውጤታማ ዘዴ ጉድለት እንዲሁም ዝርዝር መረጃን የያዙ ዘርፍ-ተኮር የጤና እና የደህንነት መረጃዎች አለመኖር የነዚህን ደረጃዎች ስኬታማ ተግባራት አደናቅፏል። የሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2010 46,000 ምርመራዎችን ያጠናቀቀ ሲሆን፣ አስተማማኝነት የሌላቸውን ሁኔታዎች ለይቶ የማወቁ ሃላፊነት በሰራተኛ ተቆጣጣሪዎች ላይ ማረፉ ግልፅ ነበር።

በክፍያ-የሰራተኛ ቅጥር እድል ያገኘው በከተሞች አካባቢ የተከማቸው የህዝቡ አነስተኛ መቶኛ መጠን ያህሉ ብቻ ነው፡፡ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ ውስጥ የሚፈፀሙ ክፍያዎች በአብዛኛው ሕይወትን ከማቆያ ደረጃዎች በታች ናቸው፡፡

በወቅት ላይ የተመሰረቱ የግብርና ሰራተኞች የካሳ ክፍያ፣ ጥቅማጥቅሞች እና የሥራ ሁኔታዎች በማህበር ከታቀፉ ቋሚ የግብርና ተቀጣሪ ሰራተኞች እጅግ ያነሱ ናቸው፡፡መንግስት ህጉን ለማስከበር የፈፀመው ተግባር አነስተኛ ነው፡፡ በመደበኛው ዘርፍ አብዛኞቹ ሰራተኞች በሳምንት 39 ሰዓታት ነው የሚሰሩት። ብዙዎቹ የውጭ ሐገር፣ የሥደተኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የጉልበት ሰራተኞች በሳምንት ከ48 ሰዓታት በላይ ይሰራሉ፡፡

የሐገሪቱ ኢኮኖሚ ዋነኛ መሰረት በሆነው የግብርና ዘርፍ ውስጥ አደገኛ የስራ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ስለ ሞት እና ጉዳቶች የሚገልፁ መረጃዎች ባይገኙም በግንባታና በኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ አደገኛ እና በዝባዥ የሥራ ሁኔታዎች እንዳሉ የሚገልፁ ሪፖርቶችም አሉ።